አፕድ አዲስ ዘመን

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 227 ሚያዝያ 17 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

“የታሪክ ስብራትን በሀገራዊ ምክክር፣ በሽግግር ፍትሕና በተሐድሶ መጠገን ይገባል”

- የብሔራዊ የደኅንነት ምክር ቤት

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- የታሪክ ስብራትን በሀገራዊ ምክክር፣ በሽግግር ፍትሕና በተሐድሶ መጠገን እንደሚገባ የብሔራዊ የደኅንነት ምክር ቤት አስታወቀ፡፡

ምክር ቤቱ በወቅታዊ ሀገራዊ የደኅንነትና ፀጥታ ጉዳዮች ዙሪያ በመምከር ትናንት በሰጠው መግለጫ፤ ነባሩን ፖለቲካዊ ችግር በሀገራዊ ምክክር፣ የቅርብ ዘመኑን የፖለቲካ ችግር ደግሞ በሽግግር ፍትሕ እና በተሐድሶ ማረም እንደሚገባ አስታውቋል፡፡

በኢትዮጵያ አንድ መንግሥት በምርጫ አሸንፎ ሥልጣን ቢይዝም እንኳን ብቻውን ሊወስናቸው የማይገቡ ሀገራዊ እና አካታች ምክክር የሚፈልጉ ጉዳዮች በመኖራቸው ይሄንን የሚያሳልጥ ገለልተኛ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ ወደሥራ ተገብቷል ያለው መግለጫው፤ ኮሚሽኑ በ10 ክልሎችና በሁለት የከተማ አስተዳደሮች ከየወረዳው በምክክሩ ሂደት የሚሳተፉ ተሳታፊዎችን የመለየት ሥራ ያጠናቀቀ ሲሆን፤ ከ679 ወረዳዎች 12 ሺህ 294 ተሳታፊዎች መለየታቸው በመግለጫው አመልክቷል፡፡

“የታሪክ ስብራትን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ሁለት ዘመናዊ የአውሮፕላን መለዋወጫና ጥገና ማዕከላት ወደ ሥራ ሊገቡ ነው

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተጨማሪ ሁለት ዘመናዊ የአውሮፕላን መለዋወጫና ጥገና ማዕከላትን ወደ ሥራ ሊያስገባ መሆኑን ዋና ሥራ አስፈጻሚው አቶ

ሁለት ዘመናዊ የአውሮፕላን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

በክልሉ ከ27 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የጤና መድን አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል

ገጽ 4

የኮሪደር ልማቱ የመዲናዋን ሁለንተናዊ እድገት የሚያረጋግጥ ነው

አማን ረሺድ

አዲስ አበባ፡- የኮሪደር ልማት ሥራው የመዲናዋን ሁለንተናዊ እድገት የሚያረጋግጥ መሆኑን በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የከተማ ዲዛይንና ፕላን ምሑሩ ዳንኤል ሊሬቦ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡ ፕሮጀክቱ በተያዘለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ ኅብረተሰቡ ድጋፉን ሊያጠናክር እንደሚገባም አመልክተዋል፡፡

ዳንኤል (ዶ/ር) ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በአዲስ አበባ እየተሠራ ያለው የኮሪደር ልማት የመዲናዋን ውበት፣ ኢኮኖሚና የነዋሪዎችን የአኗኗር ዘይቤ ለማሻሻል የሚያስችል ነው፡፡

ይህ የኮሪደር ልማትም ከተማዋን የሚመጥን፤ ዘመኑን የሚዋጅ፤ የመሠረተ ልማት አቅርቦት ለማሳደግ እንዲሁም የቱሪዝም ማዕከል ለማድረግ ያስችላል። ከዚህ አኳያም ለፕሮጀክቱ መሳካት ሁሉም አካላት

የኮሪደር ልማቱ የመዲናዋን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

አቶ ሰለሞን ስለሺ

አገልግሎቱ አንድ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር ሰበሰበ

- አንድ ሺህ 200 ሐሰተኛ ሰነዶች ጥቅም ላይ እንዳይውሉ አድርጓል

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት አንድ ሚሊዮን 237 ሺህ 329 ተገልጋዮችን በማስተናገድ አንድ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር መሰብሰቡን የፌዴራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት አስታወቀ። አገልግሎቱ አንድ ሺህ 200 ሰነዶች ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ማድረጉንም ገልጿል።

የፌዴራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሰለሞን ስለሺ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ አገልግሎቱ የቴምብር ቀረጥ እና የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል። በዚህም በ2016 በጀት ዓመት ባለፉት ዘጠኝ ወራት አንድ ሚሊዮን 237 ሺህ 329 ተገልጋዮችን በማስተናገድ አንድ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር ሰብስቧል።

አገልግሎቱ በዘጠኝ ወራት ከ715 ሺህ 500 በላይ ልዩ ልዩ የውል ሰነዶችን ማረጋገጥ ችሏል። በቀን በአማካኝ ስድስት ሺህ 400 ተገልጋዮች ይስተናገዳሉ ያሉት አቶ ሰለሞን፤ በዚህ ሂደት ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ግለሰቦች ሐሰተኛ ሰነዶችን ይዘው ወደ አገልግሎቱ መምጣታቸውን ገልጸዋል።

አንድ ሺህ 200 የማንነት ማረጋገጫ መታወቂያና የጋብቻ ማስረጃዎች ሐሰተኛ ሰነዶች በመሆናቸው ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ተደርገዋል ያሉት አቶ ሰለሞን፤ ከዚህ ውስጥ 996 የማንነት ማረጋገጫ መታወቂያዎች፣ 165 የጋብቻ ማስረጃዎች እና ቀሪው ልዩ ልዩ የውል ሰነዶች ናቸው። በዚህም 28ቱ ለፖሊስ ቀርበው ሦስት ክስ ተመስርቶባቸዋል ብለዋል።

አብዛኛው ሐሰተኛ ሰነድ የአዲስ አበባ የቀድሞውን መታወቂያና ያላገባ ማስረጃ አስመስለው ለመሥራት የተደረጉ መሆናቸውን ከተያዙ ሰነዶች መረዳት ተችሏል ያሉት አቶ ሰለሞን፤ እነዚህ ማስረጃዎች የቀሩና በቴክኖሎጂ አሠራር የተተኩ በመሆናቸው በቀላሉ ሊያዙ ችለዋል ብለዋል።

አገልግሎቱ ከፍትሕ ሥርዓቱ ጋር በተያያዘ ወንጀሎችን ለመከላከል በቀን ከስድስት ሺህ በላይ ሰነዶች ሕጋዊነታቸው ይረጋገጣል ያሉት አቶ ሰለሞን፤ በአሁኑ ወቅት ሐሰተኛ ሰነድን በመጠቀም የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለመከላከል ከባንኮች እና ከተለያዩ አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የአገልግሎቱ ሰነዶች ለባንኮች፣ ለመሬት አስተዳደር፣ ለመኪና ሽያጭ ውሎች፣ ለፍትሕ አካላት እና ለተለያዩ ተቋማት ማስረጃነት እንደሚያገለግሉ የጠቆሙት አቶ ሰለሞን፤ የአገልግሎቱ ሰነዶች "ባር ኮድ" እንዲኖራቸው በማድረግ በቀላሉ ተመሳስለው እንዳይሠሩና ሰዎች እንዳይጭበረበሩ ተደርጓል ብለዋል።

እንደ አቶ ሰለሞን ገለፃ፤ የአገልግሎቱ አሠራር በዲጂታል እየታገዘ ነው። የሰነድ ጉዳይ ትልቅ ትኩረት የሚሻ በመሆኑ ሰነዶች በአግባቡ ሊያዙና ሊፈተሹ ይገባል። ይህም ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች የበኩሉን አስተዋፅዖ ያደርጋል። ከዚህ አንፃር የአገልግሎቱ ሐሰተኛ ሰነዶችን የማረጋገጥ አቅም ተጠናክሯል።

በቀጣይም ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ትስስር በመፍጠር ችግሩን ለመቅረፍ እንደሚሠራም ገልጸው፤ በሐሰተኛ ሰነድ ሐሰተኛ ማንነት የሚቀርብበት ሁኔታ በዘላቂነት ለመፍታትም ከብሔራዊ መታወቂያ ፕሮግራም ጋር በጥምረት እየሠራ ነው ብለዋል።

በ2015 በጀት ዓመት ለአገልግሎት ቀርበው የተያዙና አገልግሎት እንዳይሰጥባቸው የተደረጉ የማንነት ማረጋገጫ መታወቂያ አንድ ሺህ 509፣ የጋብቻ ማስረጃዎች 178 እና ሌሎች ልዩ ልዩ ሰነዶች 36 በድምሩ አንድ ሺህ 723 ሐሰተኛ ሰነዶች መያዛቸውን ተናግረዋል።

አገልግሎቱ አምና ለአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ለሚሆኑ ተገልጋዮች አገልግሎት መስጠት መቻሉን የጽሕፈት ቤት ኃላፊው አቶ ሰለሞን ስለሺ አውስተዋል።

ስምምነቱ 40 ሚሊዮን ዜጎችን የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ተጠቃሚ ያደርጋል

መስከረም ሰይፉ

አዲስ አበባ፡- ስምምነቱ 40 ሚሊዮን ዜጎችን የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ተጠቃሚ እንደሚያደርግ የኢትዮጵያ ባንኮች ማኅበር አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ባንኮች ማኅበር የዲጂታል መታወቂያ ምዝገባን ለመተግበር የዲጂታል መታወቂያ ቁሣቁስ አቅራቢ ከሆነው ላሚኖ ኢንጂነሪንግ ጋር ቁሣቁሦችን ለመግዛት በትናንትናው እለት የግዥ ውል ተፈራርሟል ፡፡

የኢትዮጵያ ባንኮች ማኅበር የቦርድ ሊቀመንበር አቶ አቤ ሳኖ እንደገለጹት ስምምነቱ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ግቦችን ለማሳካት ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ በማድረግ 6ሺህ የምዝገባ ቁሣቁሦች ለመግዛት የተደረገ ነው፡፡

ይህ የግዢ ውል ስምምነት በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በ11ሺህ የባንክ ቅርንጫፎች 40 ሚሊዮን ዜጎችን የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው ብለዋል፡፡

አቶ አቤ ይህንን ውል ስምምነት ለመፈጸም ዓለም አቀፍ ጨረታ ወጥቶ አምስት ተቋማት ቢወዳደሩም ላሚኖ ኢንጂነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ማሸነፉን ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም ጨረታውን አሸንፎ ውል የተፈራረመው ተቋም በውል ስምምነቱ መሠረት ቁሣቁሶችን በወቅቱ በማቅረብ ኃላፊነቱን እንዲወጣ ሊቀመንበሩ አሳስበዋል፡፡

የፕሮጀክቱ አስተባባሪ አቶ ዮዳሔ አርዓያሥላሴ በበኩላቸው በስምምነቱ መሠረት በቀጣይ ወደ ሥራ የሚገባው ግዥ የፋይዳ ዲጂታል መታወቂያ በፋይናንስ ዘርፉ ተደራሽ እና አካታች እንዲሆን ከማስቻል ባለፈ ደኅንነቱ የተጠበቀ እና ቀልጣፋ የፋይናንስ ሥርዓትን ለማረጋገጥ ጉልህ ሚና ይጫወታል ብለዋል፡፡

በባንኮች የሚኖረው ስድስት ሺ የመመዝገቢያ ማሽኖችም በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ምዝገባውን ተደራሽ ለማድረግ ያስችላል ብለዋል፡፡ ::

አቶ ዮዳሔ ስምምነቱ በኢትዮጵያ ማንነትን የሚያረጋግጥ ሰነድ በማጣት ምክንያት በፋይናንስ ዘርፍ ላይ ያልተካተተው 30 በመቶ በላይ የሚሆነው የሀገሪቱ ነዋሪ በፋይናንስ ሥርዓት እንዲካተት አቅም እንደሚፈጥር ገልጸው፤ የፋይናንስ ዘርፍ ውስጥ ለተካተቱ 40 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ደንበኞች ቀልጣፋ፣ ተዓማኒ እና የተሻሻለ የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎቶችን ለማድረስም ጥቅሙ የጎላ መሆኑ ጠቅሰዋል፡፡

ይህም የፋይዳ ዲጂታል መታወቂያን በፋይናንስ ዘርፍ መተግበር በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ ግልጽነትን እና አካታችነትን ለማጎልበት ትልቅ ሚና የሚጫወት መሆኑን አመልክተው፤ በቁሳቁሶቹ ላይ የሚያስፈልገውን የሶፍትዌር መጫን እና ማዘጋጀት ሒደት የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮግራም የሚያከናውን ይሆናል ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ባንኮች ማኅበር 32 ባንኮችን በአባልነት አካቶ መያዙም ተገልጿል፡፡

ፎረሙ የሁለቱ ሀገራት ዜጎች በንግድና ኢንቨስትመንት በጋራ እንዲሠሩ ዕድል ይፈጥራል

አመስወርቅ ከበደ

ወይዘሮ መሰንበት ሸንቁጤ

አምባሳደር ጆርጅ ኦሪያና

አዲስ አበባ፡- የንግድ ፎረሙ የኢትዮጵያ እና የኬንያ ዜጎች በንግድና ኢንቨስትመንት በጋራ እንዲሠሩ መንገድ እንደሚከፍት የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ገለጸ፡፡

የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እና የኬንያ አምራቾች ማኅበር በጋራ ያዘጋጁት የንግድና ኢንቨስትመንት ፎረም ከትናንት ጀምሮ ለሦስት ቀናት እየተካሄደ ነው፡፡

የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሰንበት ሸንቁጤ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ የፎረሙ ዓላማ የሁለቱ ሀገራት ዜጎች በንግድና ኢንቨስትመንት በጋራ የሚሠሩበትን መንገድ ለማመቻቸት ነው፡፡

በፎረሙ ላይ የኬንያ ኢንቨስተሮች እና በአምራች ዘርፍ የተሠማሩ ባለሀብቶች መገኘታቸውን የገለጹት፤ ፕሬዚዳንቷ፤ ኢትዮጵያ ይበልጥ በአምራች ዘርፍ ለመሠማራት ፍላጎት ያላት በመሆኑ ፎረሙ የልምድ ልውውጥ ለማድረግ ያግዛል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

የኬንያ ፓርላማ አባላት በፎረሙ መገኘታቸውን ጠቁመው፤ ይህም የፓርላማ አባላቱ በንግድና ኢንቨስትመንት ዘርፍ መቀየር የሚገባቸውን ሕጎችና አዋጆች ከንግድ ማኅበረሰቡ ቀርበው በመስማት እንዲሻሻሉ አብረው ለመሥራት የሚያስችላቸው ዕድልም ይፈጥራል ብለዋል፡፡

ይህን እንደግብዓት በመውሰድ ምክር ቤቱ በቀጣይ በፓርላማው ለመሳተፍ ጥያቄ እንደሚያቀርብ እና ምክር ቤቱ ዓለም አቀፍ ተቋም እንደመሆኑ በአፍሪካ ጎብረት እና በሌሎች በዓለም ሀገራት በሚካሄዱ ጉዳዮች የኢትዮጵያን የግል ዘርፍ ወክሎ ለመሳተፍ አሳብ እንዳለው ገልጸዋል፡፡

ወይዘሮ መሰንበት እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ እና የኬንያ የንግድ ግንኙነት ሲነጻጸር ኬንያ ከ60 በመቶ በላይ ምርቶቿን ወደ ኢትዮጵያ ትልካለች፡፡ ከኢትዮጵያ ምርቶችን ወደ ኬንያ የምትልክ ቢሆንም ከኬንያ ጋር ሲነጻጸር በጣም አነስተኛ ነው፡፡

በቀጣይ ይህ እንደዚህ አይቀጥልም። ኢትዮጵያ ወደ ኬንያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካን ነፃ የንግድ ቀጣና በመጠቀም ወደ ሌሎች አገራት ምርቶቿ ለመላክ መሥራት ይኖርባታል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የኬንያ አምባሳደር ጆርጅ ኦሪያና በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ፎረሙ የኢትዮጵያ እና የኬንያ መንግሥት ባደረጉት ስምምነት መሠረት፣ የኬንያ ባለሀብቶች በንግድና ኢንቨስትመንት በኢትዮጵያ ያሉ ዕድሎችን እንዲረዱ ያስችላል፡፡

የሁለቱ ሀገራት የንግድ ግንኙነት አሁንም በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ከዚህ የበለጠ ማደግ ይችላል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

የሁለቱ ሀገራት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ተገናኝተው በተወያዩበት ወቅት በሁለቱ ሀገራት የሚደረገው የንግድ ሁኔታ ዝቅተኛ እንደሆነ የተገለጸ መሆኑን አውስተው፤ በዚህም የሁለቱን ሀገራት የንግድ እንቅስቃሴ እንዴት ማሳደግ ይቻላል በሚሉ ጉዳዮች ከንግድ ማኅበረሰቡ ጋር እየተሠራ ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

አቶ ጫላ ፈይሳ

ከግንቦት አንድ ጀምሮ የሦስተኛ ወገን መድን ሽፋን አገልግሎት ዲጂታላይዝድ ይደረጋል

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- ከግንቦት አንድ ጀምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሦስተኛ ወገን መድን ሽፋን አገልግሎት ዲጂታላይዝድ እንደሚደረግ የመንገድ ደኅንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት አስታወቀ፡፡

በፌዴራል መንገድ ደኅንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት የድኅረ ትራፊክ አደጋና መድን አስተዳደር መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጫላ ፈይሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ተቋሙ አገልግሎቱን ቀልጣፋ እና የመረጃ አያያዙን በማዘመን በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት ለመስጠት የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ ይገኛል፡፡

አገልግሎቱ በተለይም ሦስተኛ ወገን መድን ሽፋን እና የአስቸኳይ ሕክምና ተዘዋዋሪ ፈንድ አገልግሎትን ለማዘመን ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመሆን አዲስ ሶፍትዌር አልምቷል ብለዋል፡፡

አቶ ጫላ፤ ተቋሙ የተለያዩ ሥልጠናዎችን በመስጠት በሚያዚያ ወር 2016 ዓ.ም የሙከራ ትግበራው በአዲስ አበባ እና በሸገር ከተማ መደረጉን ገልጸው፤ እስካሁን በሥርዓቱ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡን ተናግረዋል፡፡

በሙከራ ትግበራው ያጋጠመ ችግር ባለመኖሩ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዷል ያሉት አቶ ጫላ በግንቦት ወር መጀመሪያም በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ እንደሚሆን ተናግረዋል፡፡ የሚያጋጥሙ ችግሮች ካሉም ማሻሻያዎች እየተደረጉ የሚቀጥሉ ይሆናል ብለዋል፡፡

ይህ የአሠራር ሥርዓት አራት ዋና ዋና ችግሮችን እንደሚቀርፍ የተናገሩት አቶ ጫላ፤ የመጀመሪያው የሦስተኛ ወገን ተለጣፊ በፌዴራል ደረጃ ታትሞ ተደራሽ ለማድረግ ረጅም ጊዜ የሚወስድና በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የሚወጣበት ነበር። አሁን ግን ሥርዓቱ አንድ ሰው ባለበት ሆኖ ክፍያ በመፈጸም አገልግሎት ማግኘት የሚያስችለው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ተቋሙ በቀላሉ የተለጣፊዎቹን ተደራሽ ማድረግ የሚያስችል እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

ሁለተኛው ለካሳ ክፍያ ከተገልጋዮች የሚሰበሰበውን አረቦን ክፍያ ከዚህ ቀደም ረጅም ሂደት የነበረው ሲሆን ሥርዓቱ ክፍያውን በቀላሉ በቀጥታ ወደ ተቋሙ እንዲገባ የሚያደርግ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ ሌላው ሥርዓቱ የነፃ አስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት ክፍያ እና አደጋ ሲደርስ በፍጥነት እና በአግባቡ መረጃ መሰብሰብ የሚያስችል መሆኑን ጠቁመዋል ::

ሥርዓቱ ከወጪ፣ ከጊዜ እንዲሁም ከመረጃ አያያዝ አንጻር የሚያመጣው ጥልቅ ለውጥ ይኖራል ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል አቶ ጫላ፡፡

በተጨማሪ ተቋሙ ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ጋር በመሆን ብሔራዊ የመንገድ ትራፊክ አደጋ መረጃ ሥርዓት (national road accident data management) የተሰኘ ሶፍትዌር አልምቶ ሙከራ ላይ ይገኛል ያሉት አቶ ጫላ፤ ይህ ሥርዓት ከዚህ ቀደም ተቋሙ ከመረጃ አያያዝ ጋር ተያይዞ ከዓለም ጤና ድርጅት ሲቀርብበት የነበረውን ቅሬታ የሚያስተካክልና በተቋሙ የሚሠሩ ሁሉንም መረጃዎች በአግባቡ የሚመዘግብ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

በብሪክስ ጥምረት የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስከብር ብሔራዊ ስትራቴጂክ እቅድ ተዘጋጀ

ሞገስ ፀጋዬ

አዲስ አበባ፡- በብሪክስ ጥምረት ውስጥ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስከብር ብሔራዊ ስትራቴጂክ እቅድ መዘጋጀቱን የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡ ብሔራዊ ስትራቴጂክ ዕቅዱ የተዘጋጀው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

በትናንትናው ዕለት ትኩረቱን በግብርናና ቴክኖሎጂ ላይ ያደረገ በብሪክስ ጥምረት ማዕቀፍ ስር የኢትዮጵያና የሩሲያ የምሑራንና የተመራማሪዎች ጉባኤ ተካሂዷል፡፡

በጉባኤው የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ጃፋር በድሩ ኢትዮጵያ ለባለብዙ ወገን ግንኙነት ልዩ ትኩረት ሰጥታ እየሠራች ነው። የኢትዮጵያና ሩሲያ ጠንካራ ግንኙነት በብሪክስ ጥምረት ማዕቀፍ ውስጥ ፍሬያማ አጋርነቶችን ለመፍጠር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ስራቴጂክ እቅድ ማውጣቱ የተጀመረው የብሪክስ አባል ለመሆን ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ጥረት በሚደረግበት ወቅት ጀምሮ ነው፡፡ ወደ ብሪክስ ማዕቀፍ ውስጥ ለመግባት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት በጋራ በመሆን እየተጠናቀቀ የሚገኝ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስከብር ብሔራዊ ስትራቴጂክ እቅድ ወጥቷል፤ ይህን ለማፅደቅ የመጨረሻውን ውሳኔ እየተጠበቀ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ውጤታማ የሆነችባቸውን የስንዴ ምርትና የሌማት ትሩፋትን ይዛ ወደ ብሪክስ ጥምረት ትገባለች ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ኢትዮጵያ ከብሪክስ አባል ሀገራት የምትወስዳቸው ስትራቴጂ፣ ፕሮጀክቶችና መደጋገፎች እንደሚኖሩ ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዝግጅትና ፍላጎት ለማድመጥ የሩሲያ የባለሙያዎች ቡድን መጥቷል ያሉት ጃፋር፤ በብሪክስ የኢትዮጵያ ፍላጎቷ ምን እንደሆነ መረጃ መሰብሰቡን ጠቅሷል፤ እንዲሁም ኢትዮጵያ በብሪክስ ማዕቀፍ ውስጥ ትኩረት በምትሰጣቸው ጉዳዮች ዙሪያ የመለየት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ከሞላ ጎደል የተጠናቀቀ አንድ ሀገር ወደ ዓለም አቀፍ ስብስብ ወስጥ ሲገባ የሚመራበት መርሕ ምንድን ነው? ምን ጥቅም ለማሳካት ነው? አቅዶችንስ እንዴት ይሳካሉ? የሚለውን በአቅድና ስትራቴጂ የተመሠረተ እንዲሆን እየሠራን ነው ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያና የሩሲያ የባለሙያዎች ጉባኤ የቅድመ ዝግጅት ውይይት ነው ያሉት አቶ ጃፋር፤ ጉባኤው ኢትዮጵያ በብሪክስ ስር በግብርና፣ ኢኮኖሚ፣ በፖለቲካው ትኩረት እንዲደረግ የምትፈልገውን ምንድን ነው? የሚለውን ለማሳወቅ የሚጠቅም መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ሞስኮ በሚካሄደው የማጠቃለያ ጉባኤ ላይ ኢትዮጵያ ቅድሚያ በምትሰጣቸው የእድገት ጉዳዮችን ለመለየት የዝግጅት ጊዜ በመሆኑ ከብሪክስ አስፈላጊውን ጥቅም ለማግኘት ይረዳታል ነው ያሉት፡፡

በብሪክስ ጥምረት ውስጥ የሩስያ የሙያተኞች ጉባኤ ኃላፊ ቪክቶሪያ ፓኖቫ (ፒኤችዲ) ጉባኤው የኢትዮጵያን ግንኙነት ይበልጥ ለማጠናከር እንደሚጠቅምም ገልጸዋል።

ሩሲያ አሁን ያለውን ትብብር ለማስፋትና በብሪክስ ጥምረት ማዕቀፍ ውስጥ ጠንካራ ግንኙነት ለመፍጠር ቁርጠኛ መሆኗን ጠቁመው፤ ይህ ውይይት ሁለገብ ትብብርን ወደ አዲስ ከፍታ ለማሳደግ ትልቅ ተስፋ እንዳለው አስረድተዋል።

የመጀመሪያ ደረጃ ውይይቶቹ ለጋራ ዕድገትና ልማት እድሎችን በመጠቀም አንገብጋቢ የሆኑ ዓለም አቀፋዊ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ የጋራ እውቀትንና ሀብቶችን የመጠቀም የጋራ ራዕይን ያንላል ብለዋል፡፡

ኮርፖሬሽኑ በአዲት ሪፖርት የተገኙ ጉድለቶችን እንዲያርም ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

ዮርዳኖስ ፍቅሩ

አዲስ አበባ፡- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ቋሚ ኮሚቴ የኢትዮጵያ ግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ኦዲት ሪፖርት የተገኙ ጉድለቶችን እንዲያስተካክል አሳስቧል፡፡ ኮርፖሬሽኑ በበኩሉ በክዋኔ ኦዲስ የተገኙ ጉድለቶችን ለማስተካከል እየሠራ መሆኑን አስታውቋል፡፡

ቋሚ ኮሚቴው የኮርፖሬሽኑን የ2014/15 በጀት ዓመት ክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ላይ በትናንትናው ዕለት ውይይት አካሂዷል፡፡

የቋሚ ኮሚቴው ዋና ሰብሳቢ ወ/ሮ የሺመቤት ደምሴ (ዶ/ር) በኮርፖሬሽኑ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት በርካታ ጉድለቶች መገኘታቸውን አስታውቀዋል፡፡

እንደ እርሳቸው ገለጻ፣ ኮርፖሬሽኑ የዘር ስርጭትና የገበያ ተደራሽነትን ሊያሰፋ ሲገባው በዝናብ ላይ ብቻ ጥገኛ ሆኖ በመሥራቱ በሚፈለገው መጠን የምርጥ ዘር ምርት ማቅረብ አልቻለም፡፡

በስትራቴጂክ እቅድ መሠረት የተለያየ ዓይነት የጓሮ አትክልት ዘሮችን ለሽያጭ ለማቅረብ ያቀደ ቢሆንም በ2012 ዓ.ም ከዕቅዱ ዜሮ ነጥብ ዜሮ ስምንት እንዲሁም በ2013 እና 2014 ዓ.ም ምንም ማቅረብ ያልቻለ መሆኑም በኦዲት ሪፖርቱ ተመላክቷል፡፡

ቋሚ ኮሚቴው የኦዲት ሪፖርቱን መነሻ አድርጎ እንደገለጸው፣ ኮርፖሬሽኑ ለደንበኞች ከሰጣቸው የዱቤ ሽያጭ ወይም የድህረ ክፍያ አገልግሎት በውል መሠረት መሰብሰብ አልቻለም፡፡

በግብርና ሜካናይዜሽን ዘርፍ ስር ከሚፈጽ ማቸው ተግባራት መካከል የቴክኒክ ሥልጠና አገልግሎት አንዱ መሆኑ የተጠቀሰ ሲሆን፣ አፈጻጸሙ ግን እጅግ ዝቅተኛ እንደሆነም ተጠቅሷል፡፡

ከ2012 እስከ 2014 በጀት ዓመት ከምርጥ ዘር እና ከአግሮ ኬሚካል ጋር በተያያዘ ከተካሄደው ምርምር በስተቀር በእርሻ መሣሪያዎች አቅርቦት ላይ የተሠራ ሥራ አለመኖሩም ኦዲት ሪፖርቱ አሳይቷል።

በኮርፖሬሽኑ የሚፈጸሙ ግዥዎች የኮርፖሬሽኑን የግዢ መመሪያ የተከተሉ አለመሆናቸው፣ ኮርፖሬሽኑ ለመጋዘን ግንባታ የሚሆን በቂ ይዞታ እያለው ለመጋዘን ኪራይ ወጪ ማውጣቱ፣ የግብርና ማሽነሪዎች አያያዝ ለብልሽት በሚዳረጉበት ሁኔታ መሆኑንና ሌሎችንም ጉድለቶች አስመልክቶ ቋሚ ኮሚቴው ማብራሪያ እንዲሰጠውና በቀጣይም አስፈላጊውን ማስተካከያ እንዲያደርግ ጠይቋል፡፡

በኮርፖሬሽኑ የግብርና ግብዓት ዘርፍ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሰሎሞን ገብሬ በበኩላቸው ኮርፖሬሽኑ ዋነኛ ዓላማው የግብርና ግብዓቶችን ለገበሬው ማቅረብ ነው ያሉ ሲሆን፣ በዚህም በርካታ ሥራዎች ማከናወኑን አንስተዋል፡፡

የኮርፖሬሽኑ የካፒታል አቅም ውስንነትና ከውጪ ምንዛሪ መዘግየትና ማነስ ጋር የተያያዙ ችግሮች ኮርፖሬሽኑ በእቅዱ ልክ እንዳይጓዝ ተግዳሮት ሆኖበታል ብለዋል፡፡

የተገኙ ጉድለቶችን የኦዲት ሪፖርቱ ከቀረበ በኋላ በማስተካከል ሂደት ላይ መሆናቸውንም አስታውቀዋል፡፡

ትዕግስት ተፈሪ

በክልሉ ከ27 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የጤና መድን አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል 27 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ዜጎች በማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድን አገልግሎት ተጠቃሚ መሆናቸውን የክልሉ ጤና ቢሮ አስታወቀ፡፡ 457 የማኅበረሰብ መድኃኒት ቤቶች አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውም ተመላክቷል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ጤና ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ትዕግስት ተፈሪ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ክልሉ የማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድን ተጠቃሚዎችን ቁጥር ለማሳደግ እየሠራ ነው፡፡ በክልሉ በማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድን አገልግሎት 29 ሚሊዮን ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 27 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

እንደሀገር ተጠቃሚ ከሆኑት ዜጎች መካከል ከ50 በመቶ በላይ የሚሆኑት በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ ናቸው ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊዋ፤ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ ዜጎችን በዝቅተኛ ክፍያ የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ለማስቻል በቀጣይም በትኩረት ይሠራበታል ብለዋል፡፡

በክልሉ የማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድን አባል መሆን ካለባቸው ዜጎች መካከል ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑትን ዜጎች አባል በማድረግ ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረጉን አስታውቀዋል።

ከማኅበረሰቡ የሚነሱትን የአገልግሎት አሰጣጥና የመድኃኒት አቅርቦት ችግሮችን ለመፍታት በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ የመድኃኒት አቅርቦት ችግርን ለመፍታት የማኅበረሰብ መድኃኒት ቤቶችን የማስፋፋት እና ከአምራች ተቋማት ጋር ያለውን ግንኙነት በማጠናከር የመድኃኒት አቅርቦት አቅማቸውን የማሳደግ ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝም አብራርተዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ 457 የማኅበረሰብ መድኃኒት ቤቶች አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን፤ ከጤና መድን አባል ውጭ ያሉ ዜጎች በማኅበረሰብ መድኃኒት ቤቱ ተጠቃሚ መሆን እንደሚችሉም ጠቁመዋል፡፡

የአገልግሎት አሰጣጥ ቅሬታን ለመፍታት የሕክምና ባለሙያዎች በምን ዓይነት ሁኔታ ያገለግላሉ የሚለውን የሚመለከቱና የማኅበረሰቡን ቅሬታ የሚቀበሉ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በየጤና ተቋማቱ መመደባቸውን ገልጸው፤ ኮሚቴው የማኅበረሰቡን ቅሬታ በመሰብሰብ ለሚመለከተው አካል አቅርበው ምላሽ እንዲሰጥባቸው እያደረጉ በመሆኑ ለውጥ ማምጣት ተችሏል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በክልሉ የጤና ተደራሽነትን ለማስፋፋትና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎች ገንዘብ የለኝም ብለው ከጤና አገልግሎት እንዳይርቁ በማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድን ተጠቃሚ ለማድረግ በቀጣይነት ይሠራል ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ በዚህም የጤና ተደራሽነትንና ጥራትን ማረጋገጥ እንደሚቻል አመልክተዋል፡፡

ኅብረተሰቡ የኢትዮ ቴሌኮምን ማኅበራዊ ገፃች በመቀላቀል ለመቄዶንያ ድጋፍ እንዲያደርግ ጥሪ ቀረበ

ሔርሞን ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- ኅብረተሰቡ የኢትዮ ቴሌኮምን ማኅበራዊ ገፆች በመቀላቀል ለመቄዶንያን አረጋውያን እና የአዕምሮ ሕሙማን ማዕከል ድጋፍ እንዲያደርግ ማዕከሉ ጥሪ ቀረበ፡፡ የትንሳኤ በዓልን ኅብረተሰቡ የምግብ ፍጆታዎች፣ የፅዳት ቁሳቁስ እንዲሁም ለበዓል የሚሆን የእርድ ከብት ይዞ በመምጣት ከአረጋውያን ጋር እንዲያሳልፉ ጥሪም ቀርቧል።

የማዕከሉ መሥራች የክብር ዶክተር ቢንያም በለጠ እንዳሉት «ሚያዚያን ለመቄዶንያ» በሚል መሪ ቃል ሁሌም ማኅበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ የሚገኘው ኢትዮ ቴሌኮም ለማዕከሉ ልዩ ትኩረት በመስጠት ለአስር ቀናት የሚቆይ የገቢ ማሰባሰቢያ ገፅ አዘጋጅቷል።

የኢትዮ ቴሌኮም የትስስር ገፆች ላይ ለሚቀላቀሉ አዳዲስ ተከታዮች ልጥፎችን በሚጋራትና ላይክ በማድረግ የሚገኘው ገቢ ለማዕከሉ እርዳታ እንደሚውል ተናግረዋል፡፡ ኅብረተሰቡም የኢትዮ ቴሌኮምን ገጽ በመቀላቀል እርዳታ እንዲያደርግም ጠይቀዋል።

በማዕከሉ ከሰባት ሺህ በላይ አረጋውያንና የአዕምሮ ሕሙማን መኖራቸውን የጠቀሱት የማዕከሉ መሥራች፤ አገልግሎቱን ወደ 20ሺህ ከፍ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

በማዕከሉ እየተሠራ የሚገኘው ባለ 15 ወለል ሕንፃ ግንባታ ላይ ኢትዮ ቴሌኮም ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

ማዕከሉ ለቀጣይ በተለያዩ ከተሞች ተመሳሳይ አገልግሎት ለመስጠት መዘጋጀቱን ገልፀው፤ በወሊሶ፣ ሱሉልታ፣ ሰበታ፣ ደብረ ብርሃን፣ ሆሳዕና እና ሌሎች ከተሞች ላይ ለመሥራት ከወዲሁ እንቅስቃሴ መጀመሩን ገልፀዋል፡፡

በሙያቸው፣ በሀሳብ እና በገንዘብ በበጎ ፈቃድ ማዕከሉን ማገልገልና መርዳት ይገባል ያሉት መሥራቹ ሠርግ፣ ልደት፣ ኒካ እና መሰል ድግሶች ከአረጋውያን ጋር በመሆን በማሳለፍ ማኅበራዊ እና ሰብዓዊ ኃላፊነት መወጣት ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የኢትዮ ቴሌኮም ማኅበራዊ ገፆች ፌስቡክ፣ ቴሌግራም፣ ኢንስታግራም፣ ዩትዩብ፣ ሊንክዲን እና ቴሌብር በመቀላቀል፤ እያንዳንዱ ሰው ሰብስክራይብ ሲያደርግ 10 ብር አዳዲስ ተከታዮች ሲቀላቀሉ 30 ብር ለመቄዶንያ ገቢ እንደሚደረግ በመረዳት ቀላል የሚመስለው ትልቅ ትርጉም የሚሰጠው እርዳታ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

“የታሪክ ስብራትን በሀገራዊ ምክክር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ምክክሩ የጉዳዩ ባለቤት የሆነውን ሕዝብ ማዕከል ያደረገ ሲሆን፤ አጀንዳዎች እና የመፍትሔ ሐሳቦች ከላይ ወደታች ብቻ ሳይሆን ከማኅበረሰቡም ፊልቀው፣ በውይይት ዳብረው ወደ መሐል የሚመጡበት አካሄድ ነው። በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ኮሚሽኑ በክልል ደረጃ የሚደረጉ የምክክር መድረኮችን ማካሄድ እንደሚጀምር እና የተሳታፊ ልየታ ባልተደረገባቸው ሁለት ክልሎች ላይ የተሳታፊዎች ልየታ በቅርቡ እንደሚጀመር ተጠቁሟል::

ይሄንን በትውልድ መካከል አንዴ የሚገኝ ዕድል ባለማባከን፣ በመደገፍና በማቃናት ለኢትዮጵያ ነባር ችግሮች መፍትሔ አዋላጅ እንዲሆን ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባየብሔራዊ የደኅንነት ምክር ቤት በመግለጫው አስታውቋል::

የሽግግር ፍትሕን በተመለከተ ኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች በደል፣ ግፍ እና መሠረታዊ የሙብት ጥሰቶች ተከስተዋል:: እስከዛሬ ባለው አካሄድ በጉልበት አሸናፊ ሆኖ ሥልጣን የያዘው አካል፣ ሌሎችን በዳይ እና አጥፊ አድርጎ በመኮነን ይቀጣል። የቁርሾ እና የቂም በቀል አዙሪት፣ የተበዳይነት እና የብሶት ትርክት በሀገሪቱ ዋነኛው የፖለቲካ ማጠንጠኛ መሆኑንም በመግለጫው ተመላክቷል::

ይሄንን የበዳይ ተበዳይ አዙሪት ለመስበር የሽግግር ፍትሕ አንዱ ተመራጭ ስልት በመሆኑ የሽግግር ፍትሕ ሂደት የሚመራበት የፖሊሲ ማዕቀፍ ፀድቋል ያለው መግለጫው፤ የፖሊሲው ዓላማም የሽግግር ፍትሕ ሂደት የሚመራበት እና የሚተገበርበትን ሥርዓት በመዘርጋት ዘላቂ ሠላምን፣ ዕርቅን፣ የሕግ የበላይነትን፣ ፍትሕን እና ዴሞክራሲን ማረጋገጥ መሆኑን በመግለጫው ተጠቅሷል።

ይሄንን ዓላማ ለማሳካት እንደ አግባብነቱ የወንጀል ምርመራ እና ክስ፣ እውነት ማፈላለግ፣ ዕርቅ፣ በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ምሕረት፣ ማካካሻ እና ተቋማዊ ማሻሻያ እንደ ሽግግር ፍትሕ ስልቶች በሀገራችን ተግባራዊ እንደሚደረጉ ተመላክቷል::

በሌላ በኩል በሀገሪቱ ከመንግሥት ውጭ ሌላ ታጣቂ ኃይል እንዳይኖር በሕገ መንግሥቱ የተቀመጠ ቢሆንም በወረስነው የፖለቲካ ስብራት የተነሣ የታጠቁ ኃይሎች መፈጠራቸውን የገለጸው መግለጫው፤ ዘላቂ ሠላምን ለማስፈን እነዚህ የታጠቁ ኃይሎች ትጥቅ ፈትተው፣ የተሐድሶ ሂደት ውስጥ መቀላቀል አለባቸው። ለዚህም የተሐድሶ ኮሚሽን ተቋቁሟል።

ዓላማውም መሣሪያ ማስፈታት፣ የታጠቁ ቡድኖችን ሠላማዊ ማድረግና ከማኅበረሰቡ ጋር መቀላቀል ናቸው። ይሄንን የተሐድሶ ሥራ በማሳካት ፖለቲካችን ከግንባር ወደ ጠረጴዛ፣ ከጫካ ወደ አዳራሽ እንዲመለሱ በማድረግ በምሕረት፣ በይቅርታ፣ በካሣና፣ በፍትሕ በመታከም ወደፊት መጓዝ እንደሚገባ በመግለጫው ተነስቷል::

በፕሪቶሪያ ስምምነት እንደተገለጸውና በሕገ መንግሥቱ እንደተደነገገው እንደ ሀገር የሚኖረው አንድ የመከላከያ ሠራዊት ብቻ ሲሆን፣ ክልሎች በክልል ደረጃ ሕግ ለማስከበር ከሚያስፈልጋቸው ፖሊስ እና ሚሊሺያ ያለፈ የታጠቀ እና የተደራጀ ሠራዊት ሊኖራቸው አይገባምም ያለው መግለጫው፤ በዚህ መሠረት ትጥቅ መፍታት እና ተያያዥ ሂደቶች በተሐድሶ ኮሚሽኑ ዕቅድ መሠረት በፍጥነት ሊተገበሩ እንደሚገባ ተመላክቷል::

በአንዳንድ አካባቢዎች የሚታዩትን ጽንፈኛ የፖለቲካ አመለካከቶች፣ የተደራጁ የወንጀል እና የዘረፋ ፍላጎቶች ለመቆጣጠር መንግሥት የሕግ አስከባሪ ተቋማትን የማሻሻል፣ ቅንጅታቸውን እና ከሕዝብ ጋር ያላቸውን ትሥሥር እንዲያጠናክሩ ሰፊ ሥራ እየሠራ ነው:: በዚህም በአዲስ አበባ እና በሌሎችም የሀገሪቱ ትላልቅ ከተማዎች የተለያዩ የሽብር ጥቃቶችን ለመፈጸም አቅደው የሚንቀሳቀሱ ኃይሎችን ዕቅድ ማክሸፍ መቻሉ ተነስቷል::

በቀጣይም ፖለቲካ ቅብ የሆኑ የተደራጁ የዝርፊያ እና የወንጀል ቡድኖችን በሚገባ ለመቆጣጠር ጠንካራ እና ውጤታማ ሕግ አስከባሪ እና የፀጥታ መዋቅር እንዲኖረን ማድረግ ተገቢ በመሆኑ ሕዝቡ ከሕግ አስከባሪ አካላት ጋር በመተባበር የሕግ የበላይነትን ማስከበር ይገባዋል ብሏል መግለጫው።

በየአካባቢው የሚገኙ የፖለቲካ እና የአስተዳደር መዋቅሮችም፣ ሌላ አካል መጠበቅ ሳይሆን፣ ሕግን ማስከበር ቀዳሚ ኃላፊነታቸው እንደሆነ ተገንዝበው ሊንቀሳቀሱ ይገባል ነው የተባለው::

አካታች የሆነ መንግሥታዊ እና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት ውጤታማ ለማድረግ፣ በሀገሪቱ ዘላቂ ሠላምና ዘላቂ ብልጽግና ለማምጣት አዲስ የፖለቲካ ባሕል የግድ በመሆኑ ሁሉን አካታች ሀገራዊ ምክክር፣ የሽግግር ፍትሕ እና የተሐድሶ ተግባራት የዚህ ማከናወኛ ዋነኞቹ መሣሪያዎች መሆናቸውን በመረዳት ድጋፍ ማድረግ እንደሚገባ ተገልጿል::

የኮሪደር ልማቱ የመዲናዋን ሁለንተናዊ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ያሳዩትን ድጋፍ ሊያጠናክሩ ይገባል::

የኮሪደር ልማት መሰል የከተማ ሞዴል በዓለም ከተሞች ተተግብሮ ውጤታማ መሆኑን ገልጸው፤ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ መሆኑ አዲስ አበባን በዘመናዊ የከተማ ፕላን በመምራት ከሌሎች ሀገራት ከተሞች ጋር ተወዳዳሪ ያደርጋታል ብለዋል::

የኮሪደር ልማቱ የመዝናኛ ቦታዎችና ሰፋፊ የአግረኛ መንገዶች የሚያካትት መሆኑ መዲናዋን ማራኪና ሳቢ ለማድረግ እንደሚያስችልም አስረድተዋል::

አዲስ አበባ ከተማ የአፍሪካ መዲናነቷን ይዛ እንድትቀጥል ምቹና ዘመናዊ መሠረተ ልማቶችን መዘርጋት እንደሚገባ ጠቁመው፤ ቀጣዩ ትውልድ ውብ ከተማን መረከብ እንዲችል ፕሮጀክቱ ትልቅ ፋይዳ ያለው በመሆኑ አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል::

ከተማዋ ካለባት የመሠረተ ልማት እጥረትና የሕዝብ ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ ዘመናት ያስቆጠሩ መሠረተ ልማቶችን ለማዘመን፣ ለማደስና የነዋሪዎችን ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የተጀመረው ሥራ ጥሩ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ዳንኤል (ዶ/ር) ጠቁመዋል::

የተጀመረው የኮሪደር ልማት ሥራ ለረዥም ዓመት እንዲያገለግል ተጠንቶ እየተገነባ የሚገኝና አዲስ አበባ ከተማን ወደ ተቀናጀ የከተማ ልማት የሚያሸጋግር መሆኑንም አመልክተዋል::

ከፕሮጀክቱ ከቅድመ ዝግጅት ጀምሮ እስከ ትግበራ ከማኅበረሰቡ ጋር ሰፊ ውይይት መደረጉን ጠቅሰው፤ ሕዝቡን ጨምሮ አመራሩ ቀንና ማታ በሥራው እየተሳተፈ ነው:: በቀጣይ ሁሉም አካላት መተባበር ይኖርባቸዋል ብለዋል::

በተጨማሪም ኅብረተሰቡ ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት ማግኘት እንዲችልና ፅዱ አካባቢ እንዲፈጠር የሚያደርግ መሆኑን ገልጸው፤ ዩኒቨርስቲው ለፕሮጀክቱ መሳካት ትልቅ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል ብለዋል::

ፕሮጀክቱ 41 ነጥብ ሰባት ኪሎ ሜትር እንደሚሸፍን የጠቆሙት የኤሌክትሪክ፣ የውሃና የቴሌኮም አገልግሎቶችን ጨምሮ የተለያዩ መሠረተ ልማቶች ለመዘርጋት አዳጋች ሲሆን የሚሠራው ሥራ መሰል ችግሮችን እንደሚቀርፍ ዳንኤል (ዶ/ር) አስረድተዋል::

ሁለት ዘመናዊ የአውሮፕላን መለዋወጫና ጥገና ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መስፍን ጣሰው ገለጹ::

የአፍሪካ አቪዬሽን የአውሮፕላን መለዋወጫና ጥገና ተቋማት ኮንፍረንስና ኤግዚቢሽን ትላንት በአዲስ አበባ ተከፍቷል::

ዋና ሥራ አስፈጻሚው አቶ መስፍን ጣሰው በመድረኩ ላይ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በተያዘው የፈረንጆቹ ዓመት መጨረሻ ተጨማሪ ሁለት ዘመናዊ የአውሮፕላን መለዋወጫና ጥገና ማዕከላትን አገልግሎት ያስጀምራል::

ኢትዮጵያ ተጨማሪ ሁለት ዘመናዊ የአውሮፕላን አካል ክፍሎች ጥገና ኮምፖሌክስና መለዋወጫዎች ማዕከል እየገነባች ነው ያሉት አቶ መስፍን፤ በተያዘው የፈረንጆቹ ዓመት መጨረሻ ወደ አገልግሎት ለማስገባት እየተሠራ ነው ብለዋል።

የአውሮፕላን መለዋወጫና ጥገናው አየር መንገዱን ጨምሮ በአፍሪካ በተለይም በመካከለኛው ምሥራቅ ለሚገኙ አየር መንገዶች አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ የአየር ፍሬም፣ ሞተርና አካል ጥገናን ጨምሮ የምሕንድስና የቁሳቁስ አገልግሎቶችን እንደሚሰጥ አስረድተዋል።

አፍሪካ አቪዬሽን ኢንዱስትሪ ከሦስት አስርተ ዓመታት በላይ ወሳኝ ሚና ሲጫወት መቆየቱን በመግለጽ፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ከአፍሪካ አየር መንገድና አምራቾች ጋር ለመተባበር ዝግጁ መሆኑን ገልጸዋል።

በአፍሪካ በቂና አስተማማኝ የአውሮፕላን መለዋወጫና ጥገና አገልግሎት አቅራቢዎች የሉም ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ የአፍሪካ አየር መንገዶች አውሮፕላኖቻቸውን፣ ሞተሮቻቸውንና አካሎቻቸውን ወደ አውሮፓና መካከለኛው ምስራቅ እየላኩ ይገኛል ብለዋል።

አፍሪካ በአውሮፕላን መሐንዲሶችና ቴክኒሻኖች የሚሠለጥኑ ብዙ ወጣቶች እንደሚኖሩባት ጠቅሰው፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ውጤታማና ዘመናዊ የአውሮፕላን መለዋወጫና ጥገና ፋሲሊቲ እየሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

በአፍሪካ አቪዬሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ ስትራቴጂ አለመኖር፣ የውስጥ አቅሞች ደካማነት፣ የፋይናንስ አቅርቦት እጥረት መኖሩን በመግለጽ፤ ምቹ የንግድ አካባቢ አለመኖር፣ ከፍተኛ የነዳጅ ዋጋ፣ የመሬት አገልግሎት አቅርቦት፣ ከፍተኛ ግብር፣ የትራፊክ መብት ገደቦች ችግር መሆናቸውን አስረድተዋል።

የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ደንጌ ቦሩ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ የአቪዬሽን ኢንዱስትሪውን ዕድገትና ልማት በአፍሪካ አህጉር ሁሉ ለማሳደግ ቁርጠኛ ነች።

መድረኩ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመለዋወጥ በጋራ ለመሥራት የሚያስችል መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይም ለቀጣዩ ትውልድ የተሻለች አፍሪካን ለመፍጠር እንደሚያስችል ጠቁመዋል።

የአውሮፕላን መለዋወጫና የጥገና አገልግሎት አቅምና ብቃት ለማሳደግ በትብብር መሥራት ያስፈልጋል ያሉት አቶ ደንጌ፤ ኢትዮጵያ የኢንዱስትሪውን ፍላጎት በማሟላት ረገድ ስኬት እያስመዘገበች ነው ብለዋል::

ኢትዮጵያ በአፍሪካ አሕጉርና በተቀረው ዓለም መካከል ወሳኝ ትስስር ሆና እያገለገለች እንደምትገኝ ጠቅሰው፤ የአየር ትራንስፖርት ማዕከል ለመሆን ስትራቴጂያዊ ቦታ ላይ እንደምትገኝ ገልጸዋል::

እንደ አቶ ደንጌ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ለዘላቂ ልማትና ቀልጣፋ የትራንስፖርት ሥርዓት ለመዘርጋት እየተጋች ናት። የኢንዱስትሪውን ዕድገትና ልማት ለማረጋገጥ ከአየር መንገድ ባለድርሻ አካላት ጋር እየተሠራ ነው።

በተጨማሪም የአየር መጓጓዣን ደኅንነት፣ አስተማማኝነትና ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ መለዋወጫና ጥገና ወሳኝ ሚና እንዳለው በመግለጽ፤ ለኢኮኖሚ እድገት፣ ለማኅበራዊ ልማትና ለአሕጉራዊ ትብብር ቁልፍ መሆኑንም አመላክተዋል።

በመድረኩ ላይ በዘርፉ የሚሠሩ ግዙፍ ዓለም አቀፍ ተቋማት የልምድ ልውውጥ በማድረግ ሥራዎቻቸውን የሚያቀርቡ ሲሆን ለሦስት ቀናትም እንደሚቆይ ተገልጿል::

ርዕሰ አንቀፅ

የለውጥ ጉዞው የተለወጠ ማንነት፣ ጥንቃቄ፣ ትዕግስት እና ሆደ ሰፊነትን ይፈልጋል!

የአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት የሚወሰነው ለለውጥ የተነቃቃ እና ለውጥን በጠንካራ ዲሲፕሊን መሸከም የሚችል ትውልድ መፍጠር ሲቻል ነው። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ስለ ለውጥ ሆነ ከለውጥ ሊገኝ ስለሚችሉ ትሩፋቶች ማሰብ ከምኞት ያለፈ ትርጉም ሊኖረው አይችልም ።

በተለይም እንደኛ ዓይነት በትውልዶች መካከል ከፍ ያለ ተለውጦ የመታየት መሻት ባለባቸው ሀገራት፤ ለውጥን በተጨባጭ እውን ለማድረግ፤ ከሁሉም በፊት እንደ ማኅበረሰብ ራስን በአግባቡ ለማወቅ የሚያስችል ድፍረት፤ ለዚህ የሚሆን በቂ ዝግጁነት መፍጠር ያስፈልጋል ።

የአንድ ማኅበረሰብ ማንነት የሚመሠረተው በዛ ማኅበረሰብ ውስጥ ባሉ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ እሳቤዎች ነው። በነዚህ ውስጥ በዋንኛነት መንፈሳዊ እና ባሕላዊ እሴቶች ትልቁን ስፍራ የሚይዙ ናቸው። እነዚህን እሴቶች በለውጥ እሳቤ የመቃኘቱ እውነታ በለውጥ ወቅት በቂ ትኩረት የሚሻ ነው ።

እነዚህ እሴቶች ታሳቢ ያደረጉ ትርክቶች ምን ያህል ለለውጡ አቅም ስለመሆናቸው ጊዜ ወስዶ ማየት አስፈላጊ ነው። ትርክቶቹን በአግባቡ በመግራት፣ ከማኅበረሰቡ የመለወጥ መሻት ጋር ተናበው የሚሄዱበትን/ዘመኑን የሚዋጁበትን የአስተሳሰብ መሠረት መገንባትም ያስፈልጋል ።

በየትኛውም የዓለም ክፍል የተደረጉ ስኬታማ የለውጥ ፍላጎቶች፣ ለስኬታቸው እንደ ዋነኛ አቅም ተደርጎ የሚወሰደው፣የማኅበረሰቡን የቀደሙ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ እሳቤዎች በመግራት አዲሱን የለውጥ እሳቤ መሸከም የሚችሉበትን ዕድል መፍጠር በመቻላቸው ነው ።

ይህን ማድረግ ባልተቻለበት ሁኔታ፣ የትኛውም አይነት የለውጥ መነቃቃት ተጨባጭ የለውጥ አቅም ሆኖ በማኅበረሰብ ውስጥ የሚፈለገውን ለውጥ ማምጣት አይቻልም። ቢሞከር እንኳን "በአሮጌ አቁማዳ አዲስ ወይን ጠጅ" እንደሚባለው ውጤቱ ኪሳራ እንጂ ስኬት ሊሆን አይችልም። ለውጥ በባሕሪው ሰፊ ማኅበራዊ መሻቶችን የያዘ ነው፤ ብዙ ተጠባቂ ትሩፋቶችንም የተሸከመ ነው፤ ጉዞው በተለወጠ ማንነት፤ በጥንቃቄ፣ በትዕግስት እና በሆደ ሰፊነት ሊመራ ይገባል። ይህን ማድረግ ካልተቻለ ሊያስከትል የሚችለው ጥፋት ይዞት ከተነሳው ተስፋ የከፋ እንደሚሆን የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች ያመለክታሉ ።

በእኛም ሀገር በተለያዩ ወቅቶች የተደረጉ የለውጥ ንቅናቄዎች፤ በብዙ ተስፋ ታጅበው፤ ከፍ ባለ ሕዝባዊ ተሳትፎ ቢጀመሩም፤በተለወጠ ማንነት ባለመመራታቸው እና ለውጡን ሊሸከም የሚችል ማኅበራዊ የአስተሳሰብ መሠረት መገንባት ባለመቻሉ ፍጻሜያቸው በብዙ ጥፋት የታጀበ ስለመሆኑ ታሪካችን በተጨባጭ የሚዘከረው ነው ።

በቅርቡ በብዙ ተስፋ እና ሕዝባዊ መሠረት የጀመርነው ለውጥም ቢሆን በተገቢው መልኩ ለውጡን የሚሸከም ሕዝባዊ የአስተሳሰብ መሠረት መፍጠር ባለመቻላችን፤ በለውጥ ወቅት በሚያጋጥሙ መንገጫገጮች ለመፈተን የተገደደበት ሁኔታ ተፈጥሯል፤ በዚህም ለውጡን በእልልታ የተቀበሉ ግለሰቦች እና ቡድኖች ሳይቀሩ በለውጡ ላይ ጠላት የሆኑበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

እነዚህ ኃይሎች ባልተለወጠ ማንነት የለውጡ አካል እና አቅም ሆነው ለመጓዝ ያደረጉት ጥረት፤ "በአሮጌ አቁማዳ አዲስ ወይን ጠጅ" እንደሚባለው፤ ለለውጡ የቸገር ምንጭ ከመሆን ያለፈ ፋይዳ እንዲኖራቸው አላስቻላቸውም። ለራሳቸው ግራ ተጋብተው የለውጥ ወቅት ግራ መጋባት ምንጭ ሆነዋል። በዚህም ሀገር እና ሕዝብን ያልተገባ ብዙ ዋጋ አስከፍለዋል ።

ይህ በየዘመኑ ሀገርን የሚፈታተን ባልተለወጠ ማንነት የለውጥ ኃይል ለመሆን የሚደረግ ግርግር፤ “ግርግር ለሌባ ይመቻል“ እንደሚባለው ብዙ የማኅበረሰባችንን በጎ እሴቶች ለአደጋ ተጋላጭ አድርጓል። ይህ እንደ ጥላ የሚከተለን ሀገራዊ ችግር አንድ ቦታ ላይ መቆም ካልቻለ፤ የሕዝባችን የለውጥ መሻት መቼም ቢሆን ተጨባጭ እውነት ሊሆን አይችልም ።

ለዚህ ደግሞ ከሁሉም በላይ የለውጥ ባለቤት የሆነው ሕዝባችን እውነታውን በአግባቡ ሊያጤነው ይገባል። በተስፋው ላይ የሚቆምሩ ግለሰቦች እና ቡድኖችን በቃችሁ በማለት፤ መሻቱን እውን የሚያደርግበትን ሀገራዊ ዓውድ መፍጠር ይኖርበታል። ይህን በማድረግ ለራሱም ሆነ ለመጪው ትውልድ የተሻለች ሀገር መፍጠር የሚያስችል መሠረት መጣል ይኖርበታል፤ ለዚህ ደግሞ ከዛሬ የተሻለ ጊዜ የለም፤ አይኖርምም!

“የዚህ ትውልድ የሃምሳ ዓመት አጀንዳ ዘላቂ ሠላም እና ሁለንተናዊ ብልፅግና ነው“

- ብሔራዊ የደኅንነት ምክር ቤት

/በወቅታዊ ሀገራዊ የደኅንነትና ፀጥታ ጉዳዮች ዙሪያ በመምከር፣ ከብሔራዊ የደኅንነት ምክር ቤት የተሰጠ መግለጫ ሙሉቃል /

የተከበራችሁ የሀገራችን ሕዝቦች፣

ኢትዮጵያ በረጅም ዘመን የሀገረ መንግሥትነት ታሪኳ፣ የፖለቲካ ልዩነቶችን፣ አለመግባባቶችን እና ግጭቶችን በሠላማዊ መንገድ፣ በንግግር፣ በውይይት እና በሕጋዊ አግባብ የመፍታት ልምምድ የላትም። እንደ አለመታደል ሆኖ ፖለቲካችን የዜሮ ድምር ፖለቲካ ነው። በሀገራችን የተለመደው በጉልበት አሸንፎ ሥልጣን የያዘ ኃይል፣ በጉልበት ተሸንፎ ሥልጣን እስኪለቅ ድረስ ሁሉንም ጠቅልሎ የሚቆጣጠርበት እና የፈቀደውን የሚያደርግበት የፖለቲካ ባሕል ነው።

የለውጡ መንግሥት ወደ ሥልጣን የመጣው በጉልበት አይደለም። ይሄም አዲስ የፖለቲካ ባሕል ነው። ይሄን አዲስ የፖለቲካ ምዕራፍ የሚያጸና ሌላ ሠላማዊ የፖለቲካ ባሕል ደግሞ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የሕዝብ ይሁንታ አግኝቶ መንግሥት በመመሥረት አሳይቷል። ከዚህም በመሻገር ልዩ ልዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች አመራሮችና አባላትን በመንግሥት ኃላፊነት በመመደብ፣ ኢትዮጵያ የጋራ ቤት መሆንዋን አስመስክሯል።

ሠላማዊ የፖለቲካ ሽግግር ብቻውን ግብ አይደለም። ሌሎች ግቦችን ለማሳካት መሣሪያ እንጂ። የኢትዮጵያ ችግር የአሁኑን አካሄድ በማስተካከል ብቻ አይፈታም። በታሪክ ውስጥ የወረስናቸውን ስብራቶች መጠገንም የግድ ይለናል። እነዚህን የታሪክ ስብራቶች ለመጠገን ሦስት ዓይነት መፍትሔዎች ተቀምጠዋል። ነባሩን ፖለቲካዊ ችግር በሀገራዊ ምክክር መፍታት፤ የቅርብ ዘመናችንን የፖለቲካ ችግር ደግሞ በሽግግር ፍትሕ እና በተሐድሶ ማረም።

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንድ መንግሥት በምርጫ አሸንፎ ሥልጣን ቢይዝም እንኳን ብቻውን ሊወስናቸው የማይገቡ፣ ሀገራዊ እና አካታች ምክክር የሚፈልጉ ጉዳዮች አሉ። ይሄ ድምፅ መሰማት ከጀመረ ግማሽ ምዕተ ዓመት እየዘለቀው ነው። የለውጡ መንግሥት እስከመጣበት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ግን ሰሚ አላገኘም ነበር። የለውጡ መንግሥት ሐሳቡን መቀበል ብቻ ሳይሆን ይሄንን የሚያሳልጥ ገለልተኛ ተቋምም አቋቁሟል።

በዚህ ተቋም ውስጥ በኃላፊነት የተሰየሙት ከፍተኛ ልምድ እና ብቃት ያላቸው ገለልተኛ ኮሚሽነሮች ናቸው። እነዚህ ኮሚሽነሮች አካታች ሀገራዊ ምክክሩን የማከናወን ሰፊ ሥልጣን በሕግ ተሰጥቷቸዋል። በዚሁ መሠረት ባለ ድርሻ አካላትን በማማከር ሂደቱ ምን መምሰል አለበት የሚለውን ዝርዝር አካሄድ እና አሠራሩን ነድፈዋል። በአሁኑ ወቅት የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ በነደፈው አካሄድ መሠረት በ10 ክልሎች እና በሁለት የከተማ አስተዳደሮች ከየወረዳው በምክክሩ ሂደት የሚሳተፉ ተሳታፊዎችን የመለየት ሥራ አጠናቋል።

በእያንዳንዱ ክልል እጅግ ጥብቅ እና አድካሚ የሆነ ሥራ ተከናውኗል። ማኅበረሰቡን ከታችኛው የአስተዳደር መዋቅር ጀምሮ አሳትፏል። በዚህም በምክክሩ አካሄድ የሚሳተፉ ዜጎች ተለይተዋል። ከ679 ወረዳዎች፣ እስካሁን 12,294 ተሳታፊዎች ተለይተዋል።

ይሄ አካሄድ የጉዳዩ ባለቤት የሆነውን ሕዝብ ማዕከል ያደረገ ነው። አጅንዳዎች እና የመፍትሔ ሐሳቦች ከላይ ወደ ታች ብቻ ሳይሆን ከማኅበረሰቡም ፈልቀው፣ በውይይት ዳብረው ወደ መሐል የሚመጡበት አካሄድ ነው።

በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ኮሚሽኑ በክልል ደረጃ የሚደረጉ የምክክር መድረኮችን ማካሄድ እንደሚጀምር ይጠበቃል። እንዲሁም የተሳታፊ ልየታ ባልተደረገባቸው ሁለት ክልሎች ላይ የተሳታፊዎች ልየታ በቅርቡ ይጠናቀቃል። በጉጉት የሚጠበቀው አካታች ሀገራዊ ምክክር ጉባኤ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚካሄድ ተስፋ ይደረጋል። ይሄንን በትውልድ መካከል አንዴ የሚገኝ ዕድል ሳናባክን፤ እያቃናንና እየደገፍን፣ ለኢትዮጵያ ነባር ችግሮች መፍትሔ አዋላጅ እንዲሆን፣ ሁላችንም የድርሻችንን ልንወጣ ይገባናል። ዕድሎችን በሰበብ አስባቡ እያባከንን፣ ራሳችንን በችግር አዙሪት የማከረም አካሄድ ማብቃት አለበት።

ሁለተኛው የሽግግር ፍትሕ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች በደል፣ ግፍ እና መሠረታዊ የመብት ጥሰቶች ተከስተዋል። ይህ በሌሎች ሀገራት ታሪክም የሚታይ ክሥተት ነው። እስከዛሬ ባለው አካሄዳችን በጉልበት አሸናፊ ሆኖ ሥልጣን የያዘው አካል፣ ሌሎችን በዳይ እና አጥፊ አድርጎ ይኮንናል፤ ይቀጣል። ይህ አካሄድ ግን ፍትሕን አያሰፍንም።

እልህን፣ ቁጭትን እና የበቀል ጥማትን ያገነግናል እንጂ።

የቁርሾ እና የቂም በቀል አዙሪት፣ የተበዳይነት እና የብሶት ትርክት በሀገራችን ዋነኛው የፖለቲካ ማጠንጠኛ የሆነበት አንዱ ምክንያትም ይሄው ነው። ይሄንን የበዳይ ተበዳይ አዙሪት ለመስበር የሽግግር ፍትሕ አንዱ ተመራጭ ስልት ነው። ስለዚህም የሽግግር ፍትሕ ሂደት የሚመራበት የፖሊሲ ማዕቀፍ ፀድቋል።

የፖሊሲው ዝግጅት የሚመለከታቸውን አካላት ያሳተፈ፣ ዓለም አቀፍ ልምድን መሠረት ያደረገ ነው። በቅድመ ፖሊሲ ማርቀቅ ሂደቱ ብቻ 60 የክልል እና 20 ሀገራዊ የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮች ተካሂደውበታል። የፖሊሲው ዓላማ የሽግግር ፍትሕ ሂደት የሚመራበት እና የሚተገበርበትን ሥርዓት በመዘርጋት ዘላቂ ሰላምን፣ ዕርቅን፣ የሕግ የበላይነትን፣ ፍትሕን እና ዴሞክራሲን ማረጋገጥ ነው።

ይሄንን ዓላማ ለማሳካት እንደ አግባብነቱ የወንጀል ምርመራ እና ክስ፣ እውነት ማፈላለግ፣ ዕርቅ፣ በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ምሕረት፣ ማካካሻ እና ተቋማዊ ማሻሻያ እንደ ሽግግር ፍትሕ ስልቶች በሀገራችን ተግባራዊ ይደረጋሉ።

እንደሚታወቀው በሀገራችን ከመንግሥት ውጭ የሚኖር የታጠቀን ኃይል ሕገ መንግሥታችን አይፈቅድም። የመንግሥትም አንዱ መብት በብቸኝነት ኃይልን መጠቀም ነው። ነገር ግን በሀገራችን በወረሰነው የፖለቲካ ስብራት የተነሣ የታጠቁ ኃይሎች ተፈጥረዋል። ሰላማችንን የጸና ለማድረግ፣ እነዚህ የታጠቁ ኃይሎች ትጥቅ ፈትተው፣ የተሐድሶ ሂደት ውስጥ መቀላቀል አለባቸው።

የፖለቲካ ጥያቄዎቻቸውንም በሀገራዊ ምክክር ሂደት በመሳተፍ መፍታት ይችላሉ። ለዚህ የሚሆን የተሐድሶ ኮሚሽን ተቋቁሟል። ዓላማውም መሣሪያ ማስፈታት፣ የትጥቅ ቡድኖችን ሠላማዊ ማድረግና ከማኅበረሰቡ ጋር መቀላቀል ናቸው። ይሄንን የተሐድሶ ሥራ በማሳካት ፖለቲካችን ከግንባር ወደ ጠረጴዛ፣ ከጫካ ወደ አዳራሽ እንዲመለስ ማድረግ አለብን። እነዚህን ስልቶች በሚገባ ተግባራዊ በማድረግ፣ ከበዳይ ተበዳይ አዙሪት ልንወጣ ያስፈልጋል።

በምሕረት፣ በይቅርታ፣ በካሣና፣ በፍትሕ ታክመን ወደፊት መጓዝ መቻል አለብን። ለዚህ

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpressпromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

“የዚህ ትውልድ የሃምሳ ዓመት አጀንዳ ዘላቂ ሠላም...

ከገጽ 5 የዞረ

ስኬትም ኢትዮጵያውያን ሁሉ በንቃትና በብቃት ልንሳተፍ ይገባናል። መንግሥትም የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ አተገባበርን ከሀገራዊ ምክክር ሂደቱ ጋር የተናበበ እና የሚመጋገብ እንዲሆን በማድረግ ኃላፊነቱን ይወጣል።

ነባር ሀገራዊ ችግሮቻችንን በሀገራዊ ምክክር እና በሽግግር ፍትሕ እያረምን የገጠሙን የግጭትና የጦርነት ፈተናዎች ለመሻገር ደግሞ ሠላማዊ የፖለቲካ አካሄዶችን ተመራጭ ማድረግ አለብን። ለሁለት ዓመታት የዘለቀውን የሰሜኑን ጦርነት በሠላም ስምምነት ለመፍታት የተፈለገውም ለዚህ ዓላማ ነው።

በኢትዮጵያ ታሪክ በተለያዩ ወቅቶች የእርስ በርስ ግጭቶች እና ጦርነቶች በተደጋጋሚ ተከሥተዋል። በእነዚህ ጦርነቶች እንደ ሀገር ከባድ ኪሣራ ደርሶብናል። የዚህም ምክንያቱ ግጭቶችን በንግግር እና በስምምነት የመፍታት የፖለቲካ ልምምድ ብዙም ስለሌለን ነው። የለመድነው በጠላታችን መቃብር ላይ ሐውልት መገንባት ነው።

የፕሪቶሪያው የሠላም ስምምነት ይሄንን ነባር ልማድ ቀይሮታል። ጦርነትን በፖለቲካዊ መፍትሔ የመቋጨት ባሕል አምጥቷል። ይሄ የሠላም ስምምነት ለትውልድ የአሸናፊ ተሸናፊ ትርክትን ከቂም ጋር ላለማውረስ የተደረገ በሳልና ቆራጥ ውሳኔ ነው። ይሄንን አማራጭ ተከትለን፣ ደም መፋሰስ እና ግጭትን ማቆም ችለናል። በአማራ፣ በአፋርና በትግራይ ክልሎች የመልሶ ግንባታ እና የመልሶ ማቋቋም ሥራዎች ተጀምረዋል።

ሰብዓዊ ድጋፍም ያለመሰናከል ወደ ትግራይ መድረስ የሚችልበትን ዓውድ ፈጥረናል። የሠላም ስምምነቱ በተፈረመ ማግሥት መንግሥት በሠላም ስምምነቱ ከገባው ግዴታ ያለፈ፣ መተማመን ለመፍጠር እና ሠላምን ለማጽናት አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን ርምጃዎች በተከታታይ ወስዷል። በሠላም ስምምነቱ እስካሁን የተገኘው ውጤት እና እፎይታ እንደተጠበቀ ሆኖ ቀሪ ሥራዎችም አሉ።

በተለይ በስምምነቱ መሠረት የሕወሓት ታጣቂዎች ትጥቅ መፍታት አለባቸው። የማንነት እና የአስተዳደር ወሰን ጥያቄ ያለባቸውን አካባቢዎች ጉዳይ እልባት ለመስጠት እንዲቻል የተቀመጠው አቅጣጫ ተግባራዊ መደረግ አለበት። በጦርነቱ የተፈናቀሉትን ለመመለስና ለማቋቋም የተጀመረው ሥራ እልባት ማግኘት አለበት።

ካለፈ ስሕተተ አለመማር የመጀመሪያውን ስሕተት ከመሥራት የባሰ ነው። ካለፈው ስሕተታቸው ሳይማሩ ዛሬም ተመሳሳይ ችግር ለመፍጠር የሚከጅሉትን ሁላችንም ተባብረን አደብ ማስገዛት ይኖርብናል። ከትዕግሥት በኋላ የሚከሥት ሕግ የማስከበር ሥራ የሚኖረውን አስከፊ ውጤት ከቅርቡ ታሪካችን ልንማር ይገባልና።

መንግሥት የተቋረጡ መሠረት ልማቶችን እና አገልግሎቶችን ለመጠገን እና መልሶ ለማስጀመር ወገቡን አሥሮ እየሠራ ነው። የፋይናንስ እና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን በትግራይ ክልል ለማሣለጥ እጅግ ከፍተኛ ወጪ አውጥቷል። የሠላም የትርፍ ድርሻው ታላቅ በመሆኑ መንግሥት ከሚጠበቅበትም አልፎ ቁስልን ለመሻር የሚያስችል ሥራ እየሠራ ነው። ይሄ ግን መንግሥታዊ ኃላፊነት እንጂ ፍርሃት ተደርጎ መወሰድ የለበትም።

በፕሪቶሪያ ስምምነት እንደተገለጸው፣ በሕገ መንግሥታችንም እንደተደነገገው፣ እንደ ሀገር የሚኖረን አንድ የመከላከያ ሠራዊት ብቻ ነው። ክልሎች በክልል ደረጃ ሕግ ለማስከበር ከሚያስፈልጋቸው ፖሊስ እና ሚሊሺያ ያለፈ የታጠቀ እና የተደራጀ ሠራዊት ሊኖራቸው አይችልም፤ አይገባምም። በዚህ መሠረት ትጥቅ መፍታት እና ተያያዥ ሂደቶች በተሐድሶ ኮሚሽኑ ዕቅድ መሠረት በፍጥነት ሊተገበሩ ይገባል።

ወንድሞቻችን/እኅቶቻችን በተለይም ወጣቶች በተለያዩ ምክንያቶች ተገፋፍተው በጽንፈኞች እና በግጭት ጠማቂዎች ወደ ጦር ዐውድማ የሚማገዱበት አጋጣሚ አለ። መንግሥት ይሄንን ሁኔታ ከአንድ አቅጣጫ ብቻ አያየውም። እንቅስቃሴያቸው ሕገ ወጥ ስለሆነ ብቻ ጉዳዩን በጉልበት ብቻ ይፈታ ማለት እንደሌለበት ይገነዘባል።

ስለዚህ ከጥፋት መንገድ ለመመለስ እና ማኅበረሰቡን ተቀላቅለው ሠላማዊ ሕይወት ለመኖር ፍላጎት ያላቸውን ታጣቂዎች ሁሉ፣ በተዘረጋ እጅ ለመቀበል መንግሥት ፈቃደኛ ነው። ይሄንን ፈቃደኝነቱን እና ፍላጎቱን በተግባር በተለያዩ ክልሎች አሳይቷል። በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በአማራ እና በኦሮሚያ ክልሎች በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ታጣቂዎች እጃቸውን ሰጥተዋል።

እነዚህም የተሐድሶ ሥልጠና ወስደው፣ ከማኅበረሰቡ ጋር እንዲቀላቀሉ ተደርጓል። ይሄንንም በተሐድሶ ኮሚሽን በኩል ከክልሎች ጋር በመቀናጀት አጠናክረን እንቀጥላለን። ጥረቱን የሀገር ሽማግሌዎች እና የሃይማኖት አባቶች እንዲደግፉ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪ እናደርጋለን።

እነዚህን ዘላቂ መፍትሔ አምጪ ሥራዎች በአንድ በኩል እያከናወንን የሕዝቡን ሠላምና ደኅንነት የሚያስከብሩ አሁናዊ ተግባራትንም ማከናወናችንን እንቀጥላለን።

ጽንፈኛ የፖለቲካ አመለካከቶች እንዲሁም የተደራጁ የወንጀል እና የዘረፋ ፍላጎቶች በአንዳንድ አካባቢዎች እየታዩ ናቸው። እነዚህን በገጠርም ሆነ በከተማ የሕዝብን ሠላም የሚያውኩ እንቅስቃሴዎች ለመቆጣጠር መንግሥት ሰፊ ሥራ እየሠራ ነው። የዚህ ሥራ አንዱ አካል፣ የሕግ አስከባሪ ተቋማትን እያሻሻሉ፤ ቅንጅታቸውን እና ከሕዝብ ጋር ያላቸውን ትሥሥር እያጠናከሩ እንዲሄዱ ማድረግ ነው።

በገጠር ቀበሌዎች እና መንደሮች፣ የየአካባቢው ነዋሪ በአግባቡ ሠልጥኖ አካባቢያዊ ሠላሙን ለማስከበር እንዲችል ይደረጋል። በዚህ ረገድ በአንዳንድ ክልሎች በጎ ጅምር አለ። እንደ ኢትዮጵያ ላለ እጅግ ሰፊ እና ብዙ ሕዝብ ላለበት ሀገር፣ የአካባቢ ሚሊሺያ እና ሌሎች ኢጋዥ ሰላም አስከባሪ አደረጃጀቶች አካባቢያዊ ሰላም እና ፀጥታን ለማስከበር ትልቅ ሚና አላቸው።

ከዚያ በተጨማሪ፣ የክልል ፖሊስ ኃይሎችን መልሶ በማደራጀት እና በሁለንተናዊ መልኩ በማጠናከር፣ ሕገ መንግሥታዊ ተልዕኳቸውን በአግባቡ እንዲወጡ እየተደረገ ነው።

በየአካባቢው ካሉት ሚሊሺያዎች እና የክልል ፖሊሶች ጋር በመቀናጀት፣ የፌደራል ፖሊስ የሀገር ውስጥ ሠላም እና ሕግ የማስከበር ኃላፊነቱን እንዲወጣ ቀጣይነት ያለው ተቋም ማጎልታ እና ማሻሻያ እየተካሄደ ነው። ከእነዚህ ሕግ አስከባሪ ተቋማት ያለፈ ሥጋት ካጋጠመ፣ የሀገር መከላከያ ሠራዊት ሠላም የማስጠበቅ እና ሕግ የማስከበር ተግባሩን እየተወጣ ይገኛል።

ይሄንን ዓይነት የፀጥታ አካላትና የሕዝብ ቅንጅት በመኖሩ፣ በአማራ ክልል የክልሉን መንግሥት አፍርሶ በኃይል ሥልጣን ለመያዝ ያሰበው ኃይል ፍላጎቱን ለማሳካት እንዳይችል ተደርጓል። በተሠራው የሕግ ማስከበር ሥራ፣ የክልሉን መንግሥት እና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለመታደግ ተችሏል።

በኦሮሚያ ክልልም በአንዳንድ የክልሉ ዞኖች የነበረው የታጣቂ ኃይሎች ሰፊ እንቅስቃሴ እና አንዳንድ ወረዳዎችን የመቆጣጠር አዝማሚያ ተቀልብሷል። በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልልም የፀጥታና የደኅንነት ሁኔታው በእጅጉ ተሻሽሏል። በአዲስ አበባ እና በሌሎችም የሀገሪቱ ትላልቅ ከተማዎች የተለያዩ የሽብር ጥቃቶችን ለመፈጸም አቅደው የሚንቀሳቀሱ ኃይሎችን ዕቅድ ለማክሸፍም ተችሏል።

የተሠራው ሥራ ወሳኝ ቢሆንም በቂ ግን አይደለም። ፖለቲካ ቅብ የሆኑ የተደራጁ የዝርፊያ እና የወንጀል ቡድኖችን በሚገባ መቆጣጠር ይገባናል። ይሄንን ለማድረግም ጠንካራ እና ውጤታማ ሕግ አስከባሪ እና የፀጥታ መዋቅር እንዲኖረን የተጀመረው ሥራ ይቀጥላል። በዚህ ረገድ የሕዝብ ተሳትፎ እና እገዛ ወሳኝ ነው።

እየዘረፈ፣ እየነጠቀ እና እያገተ ያለን ቡድን በተለያየ ሰበብ መሸከም እና ማባባል ማብቃት አለበት። በድኽ ገንዘብ የተሠሩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማትን የሚያወድም ቡድን የማንንም ፍላጎት አያስከብርም። ሕዝቡ ከሕግ አስከባሪ አካላት ጋር በመተባበር የሕግ የበላይነትን ማስከበር ይገባዋል። በየአካባቢው የሚገኙ የፖለቲካ እና የአስተዳደር መዋቅሮችም፣ ሌላ አካል መጠበቅ ሳይሆን፣ ሕግን ማስከበር ቀዳሚ ኃላፊነታቸው እንደሆነ ተገንዝበው ሊንቀሳቀሱ ይገባል።

በአንድ በኩል ሕግ የማስከበርና ሠላምና ደኅንነትን የማጽናት ሥራ እያከናወንን፤ በሌላ በኩል ደግሞ የተፈናቀሉ ሰዎችን የመመለስ ተግባር መከናወን አለበት። ሠላምና ፀጥታ ሕዝብ ሲረጋጋ የሚፈጠሩ ሥርዓቶች በመሆናቸው። በሀገራችን በተለያዩ ምክንያቶች፣ ሰዎች ከመኖሪያ አካባቢያቸው ተፈናቅለዋል። እነዚህ ዜጎች ከመጠለያ ካምፖች ወጥተው ወደቀያቸው መመለስ ይኖርባቸዋል። በዘላቂነት ተረጋግተው ወደ መደበኛ ኑሮ መግባት አለባቸው። ይሄንን እውን ለማድረግ መንግሥት ሲተጋ ቆይቷል፣ አሁንም ሰፊ ሥራ እየሠራ ይገኛል።

ለምሳሌ በሶማሌ እና ኦሮሚያ አዋሳኝ አካባቢዎች፣ እንዲሁም በጌዴኦ አካባቢ ተፈናቅለው የነበሩ ዜጎች ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ እና ዘላቂ መኖሪያ እንዲያገኙ ለማድረግ ተችሏል። በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ለምሳሌ በራያ እና አላማጣ አካባቢ ከተፈናቀሉ ዜጎች መንግሥትን ሳይጠብቁ በማኅበረሰባዊ መተሳሰብ ብቻ በርካታዎች ወደ ቤታቸው ገብተዋል። በዚህ ሂደት የተፈናቃዮችን ጉዳይ እንደ ፖለቲካ አጀንዳ አድርገው ሊጠቀሙ የሚፈልጉ አካላት መኖራቸው ታይቷል። ተፈናቃዮች ከተመለሱ የልመናና፣ የተቃውሞ አጀንዳችን ይከስራል ብለው ይፈራሉ። እነዚህ ኃይሎች ተፈናቃዮቹ ወደ ቤታቸው እንዳይመለሱ ፕሮፖጋንዳ እና ማስፈራሪያ ይደረድራሉ።

አንዳንዴም በኃይል ጭምር የተፈናቃዮችን መመለስ ለማሰናከል ይቃጣቸዋል። መንግሥት ካለበት የሞራል እና የሕግ ኃላፊነት የተነሣ የተፈናቀሉ ዜጎች ወደ ቤታቸውና ወደ መኖሪያቸው እንዲመለሱ ማድረጉን ይቀጥላል። ከክልሎች ጋር የተጀመረው ሥራም ይጠናከራል።

ሠላምና ጸጥታን ለማደፍረስ፣ የተፈናቀሉ ወገኖች እንዳይመለሱ ለማድረግና የልማት ተግባራትን ለማሰናከል አንዱ የመዋጊያ መሣሪያ የተዛባ፣ የተሳሳተና የተመረዘ መረጃን ማሠራጨት ነው። እንደሚታወቀው የመገናኛ ቴክኖሎጂ ዕድገት ዕድልም፣ አደጋም ይዞ መጥቷል። በዚህ ዘመነ መረብ ሽኩቻ እና ፉክክር ይበዛል። ነባር ተቋማት እና ሥርዓቶች በእጅጉ ፈተና ላይ ይወድቃሉ። በዚህ ዐውድ ውስጥ ሀገራት ብሔራዊ ጥቅማቸውን ለማስከበር ያለ ይሉኝታ እና ያለ ብዙ ልጓም የቻሉትን ሁሉ ያደርጋሉ።

በዚህ ወቅት ሁኔታውን በአግባቡ በመረዳት፣ ይሄንን ማዕበል እና ወጀብ እንዴት ማለፍ አለብን የሚለውን በጥንቃቄ ተልመን ካልተንቀሳቀስን አደጋው ከባድ ነው። በዚህ ረገድ ውጤታማ ለመሆን የውስጥ አንድነት እጅግ ወሳኝ ነው። እንደ ኢትዮጵያ ያለ ትልቅ ሀገር የውስጥ አንድነት ካለው ነጥሮ ይወጣል።

እንደ ሀገር እና እንደ ሕዝብ ለአንድ ዓላማ በጋራ ከተሰለፍን ወቅቱ ሀገራችንን ከፍ ለማድረግ የራሱን በጎ አጋጣሚዎች ይዞ ይመጣል። ከተከፋፈልን ደግሞ የሀገር ሕልውና አደጋ ላይ ይወድቃል። ስለዚህም የሚመጡ መረጃዎችን መምረጥ፣ መመዘንና ማንጠር አስፈላጊ ነው። በምድር ያሸነፍናቸው ጠላቶቻችን በአየር እንዲመጡ መፍቀድ የሉብንም።

እነዚህን ሁሉ የምናከናውነው መጀመሪያ ዘላቂ ሠላም፤ በዘላቂ ሠላም በኩልም ዘላቂ ብልፅግናን ለማረጋገጥ ነው። እንደ መንግሥት ግባችን በአጭራጭ መንገድ፣ ከላይ ከላይ በሆነ እድሳት የሚመጣ ጊዜያዊ ፀጥታ አይደለም። ዘላቂ ሠላም ነው። ዘላቂ ሠላም የጦርነት አለመኖር ብቻ አይደለም።

በመርሕ እና በሥርዓት ላይ የተመሠረተ፣ በቀላሉ የማይናወጥ ሠላም ነው። ግጭትን፣ እና አለመግባባትን በሠላማዊ እና በሕጋዊ መንገድ ለመፍታት የሚያስችል አቅም እና ሥርዓት መኖር ነው። በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ በመግባባት፣ ያለፈን ቁርሾ እና የታሪክ ጠባሳን አልፎ ወደፊት ለመሄድ መቻል ነው።

ይሄንን ዘላቂ ሠላምና ዘላቂ ብልፅግና ለማምጣት አዲስ የፖለቲካ ባሕል የግድ ነው። ሁሉን አካታች ሀገራዊ ምክክር፣ የሽግግር ፍትሕ እና የተሐድሶ ተግባራት የዚህ ማዕከናወኛ ዋነኞቹ መሣሪያዎች ናቸው። ማንም እንደሚያውቀው አካታች የሆነ መንግሥታዊ እና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት ፈር ቀዳጅ እየሆንን ነው።

ይህ ጥረት ውጤታማ እንዲሆን ግን የመንግሥት ተግባር ብቻውን በቂ አይሆንም። ገዢው ፓርቲ አዲስ የፖለቲካ ባሕል ለማስተዋወቅ - አብረን እንሥራ፣ እንምከር፣ በጋራ ለሀገራችን ጉዳዮች መፍትሔ እንፈልግ እያለ ነው። አንዳንዶች ደግሞ በድሮ በሬ እያረሱ በጉልበት፣ በኃይልና በጠመንጃ መንግሥትን ጥለን ሥልጣን ጠቅልለን ካልወሰድን እያሉ ናቸው።

እንደዚህ በተቃራኒ መንገዶች ተጉዘን የተጀመሩት ጥረቶቻችን ሊሳኩ አይችሉም። የ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ባሕልን ይዞ በ22ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መሄድ ርግማን እንጂ ለውጥ አያመጣም። ጦርነት ሁላችንንም ያከስራል። ሰላም ሁላችንንም አትራፊ ያደርጋል። እኛ ከአባቶቻችን ስለጦርነት እየሰማን አደግን፤ ይበቃናል።

በእኛ ትውልድ እንኳን ሁለትና ሦስት ከባድ ጦርነቶች አለፉ። ለቀጣይ ትውልድ ግን ብልፅግናን እንጂ ቁስልን ማውረስ የሉብንም። የኢትዮጵያን ዘመናዊ የፖለቲካ ቅኝት ለሃምሳ ዓመት የበየነው የ1966ቱ አብዮት ከተከሠተ ግማሽ ምዕተ ዓመት ሆኖታል። አዙሪቱ ያልለቀቃቸው ግን አሁንም አሉ።

ካለፈው ተምረን፣ የራሳችንን እና የዘመናችንን ዓውድ ተገንዝበን፣ በራሳችን ቅኝት እና አጀንዳ ወደፊት ልንራመድ ይገባል። የዚህ ትውልድ የሃምሳ ዓመት አጀንዳ ዘላቂ ሰላም እና ሁለንተናዊ ብልፅግና ነውና።

የብሔራዊ ደኅንነት ምክር ቤት
ሚያዚያ 16 ቀን 2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ፖለቲካና ወቅታዊ

ወቅታዊ

«49ሺህ ለሚሆኑ ከስደት ተመላሾች በሀገር ውስጥ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል»

- አቶ ደረጀ ተግይበሉ-ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከልና የተመላሽ ዜጎች ድጋፍና ክትትል መሪ ሥራ አስፈጻሚ

ፎቶ፦ ስምሰም መንግሥቱ

ስምሰም መንግሥቱ

ሰዎች የመኖሪያ አካባቢያቸውን ቀይረው ኑሮአቸውን በሌላ አካባቢ የሚያደርጉት፣ ሀገራቸውንም ለቀው ወደ ተለያዩ የዓለም ሀገር የሚሰደዱት በአብዛኛው የተሻለ ኑሮን ፍለጋ ነው፡፡ የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመለከተው በተለይም ወደመካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች የሚሄዱ በቤት ሠራተኝነት ጭምር የሚሄዱ ዜጎች ዋነኛ ዓላማቸው ራሳቸውንም ሆነ ቤተሰባቸውን በኢኮኖሚ ለማገዝ በማለም ነው፡፡

ሆኖም ወደመካከለኛው ምሥራቅ የሚሄዱ ዜጎች የአብዛኞቹ የጉዞ ሰነድ ታሪክ የሚያሳየው ከመነሻ እስከ መድረሻቸው ድረስ ያለው ጉዞ ሕጋዊነትን የተከተለ አይደለም፡፡ ሕጋዊ ሆነው እንዲሄዱ በመንግሥት በኩል ምቹ ሁኔታዎች ቢኖሩም ሕጋዊ የመሆን ፍቃደኝነት በብዙዎች ዘንድ አለመኖሩ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ተቋማት ሲገልጹ ይደመጣሉ፡፡

በሚያደርጉት ሕገወጥ ጉዞ ምክንያትም በበረሃ ላይ መቅረት፣ በባህር ውስጥ መስመጥ፣ ላላስፈላጊ የገንዘብ ወጪ መዳረግ፣ ለአካላዊና ሥነልቦናዊ ጥቃት መጋለጥ እንዲሁም ለአስገድዶ መደፈር ሰለባ እና ለመሳሰሉት ችግሮች ይዳረጋሉ፡፡

ከሰሞኑ በተሰማው መረጃ እንኳን በጀልባ መስመጥ ሕይወታቸውን ያጡ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ከፍተኛ ነው፡፡ እንዲህ ያሉ እውነታዎች እየታዩ እንኳን ሰዎች ሕገወጥ ስደትን መምረጣቸው የሚያስገርም ነው፡፡

በርካታ ውጣ ውረዶችን አልፈው በለስ ቀንቷቸው ለሥራ የሚሄዱባቸው ሀገሮች ቢደርሱ እንኳን ለተለያዩ የሠብዓዊ መብት ጥሰቶች መዳረጋቸው አይቀርም፡፡ መብታቸውን እንኳን ለማስከበር ሕገወጥ መሆናቸው እንቅፋት ሆኖባቸው ለከፋ ችግር እንደሚዳረጉ በተለያየ ጊዜ የወጡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እጅግ ዘግናኝና አሰቃቂቂ የሆኑ ድርጊቶች ቢፈጸምባቸውም ሕጋዊ መፍትሄ ለማግኘት ፈጽሞ የሚታሰብ አይደለም፡፡

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ከመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ወደ ሀገራቸው የሚመለሱ ዜጎች ቁጥር እየጨመረ መምጣት የመብት ጥሰቱ መበራከት አንዱ ማሳያ ተደርጎም ይወሰዳል፡፡ ይህ ሁሉ እያለ ግን አሁንም ሕገወጥ ስደት አልቆመም፡፡

ዜጎች ሕጋዊ መንገደዱ እያለ ለምን ሕገወጥ ስደትን ይመርጣሉ የሚለው አሁንም መልስ የሚያሻው ጥያቄ ነው፡፡ በተለይም ሞትን ጨምሮ በርካታ አሰቃቂ ተግባራት እየደረሰባቸውም ቢሆን ዜጎች ከጉዞ ጀምሮ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለማለፍ ለምን መረጡ? በአሰሪዎች የሚደርሰውን ስቃይና በደል ከተበዳዮች አንደበት እየሰሙ ለምን ትምህርት ሊወስዱበት አልቻሉም? መንግሥትስ ከዚህ አስከፊ ነገር ዜጎችን ለመታደግ ምን ሠራ? የሚለው የብዙ ሰዎች ጥያቄ ነው፡፡

እነዚህንና መሰል ጥያቄዎችን ይዘን ጉዳዩ በዋነኝነት ወደሚመለከተው ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አቅንተናል፡፡ በሚኒስቴሩ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከልና የተመላሽ ዜጎች ድጋፍና ክትትል መሪ ሥራ አስፈጻሚ ከአቶ ደረጀ ተግይበሉ ጋርም ቆይታ አድርገናል፡፡ መልካም ንባብ፡፡

አዲስ ዘመን፡- በቅድሚያ የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪትን በተመለከተ ያሰውን የሕግ ጽንሰ ሃሳብ ቢያብራሩልን?

አቶ ደረጀ፡- የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት በሕግ የተደገፈ አሠራሮችን የሚከተል ሲሆን፤ የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪትን የሚመለከት አዋጅም አለው። በአዋጁ ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጠው የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ነው። ሥራ የሚለው በራሱ ከሥራና ክህሎት ጋር ይያያዛል። የሥራ ዕድሎች በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የሚፈጠሩ ናቸው። በተለይም የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪቱ መደበኛ የሆነ ፍልሰትን የሚከተል ነው።

ዜጎች ሥራውን በግላቸውም የሚያመጡት ሊሆን ይችላል። በሌሎችም በሚገኝ የሥራ ዕድል፣ ወይንም መንግሥት ከሀገራት ጋር በሚኖረው ግንኙነት በሚመቻች ዜጎች በውጭ ሀገር ሄደው ለመሥራት ፍላጎት ሲኖራቸው ተጠቃሚ የሚሆኑበት አሠራር ነው ያለው። ዜጎች ውጭ ሀገር ሄደው ለመሥራት የሚያስችላቸው መስፈርቶች በመኖራቸው መስፈርቶቹን አሟልተው ሲገኙ የሥራ ዕድሉ ተጠቃሚ ይሆናሉ።

በተለይ ደግሞ ወደ ተለያዩ የአረብ ሀገራት የሥራ ዕድል አግኝተው የሚሄዱ ዜጎች ለጉዞ ዝግጅት ከማድረጋቸው በፊት መሠልጠን ይጠበቅባቸዋል። ቀደም ሲል የነበሩ አንዳንድ መስፈርቶች ላይም ማሻሻያ ተደርጓል። ቀደም ሲል ወደ አረብ ሀገራት ለመሄድ አንዱ መስፈርት ስምንተኛ ክፍል ማጠናቀቅ የሚል ነበር። አሁን ላይ አስፈላጊ ሆኖ ባለመገኘቱ መስፈርቱ ቀርቷል። ከትምህርት ደረጃ ይልቅ የሚሰጠውን ሥልጠና ተከታትለው፣ አልፈው ወደ ሥራ የሚሄዱበት ሁኔታ ነው የተመቻቸው።

በመደበኛው አሠራር መሠረት፤ ግለሰቡ ለተቀጠረበት የሥራ ዘርፍ ብቁ ሆኖ ነው መሄድ የሚጠበቅበት። ለእያንዳንዱ የሥራ ዘርፍ የተቀመጡ መሥፈርቶችን ማሟላት ይጠበቃል ማለት ነው። ሕጋዊው መሥመርም በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በኩል ነው የሚፈፀመው። መንግሥት ለሥራ ወደ ውጭ ለሚሄዱ ዜጎች ለሚሰጠው አገልግሎትም የሚጠይቀው ክፍያ የለም።

ዜጎችን ለማነሳሳት ሆን ብለው የተዘጋጁ አንዳንድ ሕገወጥ ኤጀንሲዎች በመኖራቸው በነዚህ የሚጭበረበሩ መኖራቸውን መዘንጋት የለበትም። ከእነዚህ በተጨማሪም በደላሎችም ይጭበረበራሉ።

እነዚህ አካላት ከፍተኛ ገንዘብ በመጠየቅ ተጓጉሮች ላይ ከፍተኛ ጫና ይፈጥራሉ። ገንዘቡንም የሚጠይቁት ሩቅ ሳይሄዱ እዛው ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ደጃፍ ላይ ነው። ብዙ ገንዘብ ከፍለው የሀሰት ሰነድ እየሰጧቸው ብዙዎች ሲያለቅሱ እናያለን።

ስለዚህም ማንኛውም ወደ ውጭ ለመሄድ የሚፈልግ ዜጋ እራሱን ከእነዚህ ሕገወጥ ደላሎች መጠበቅ አለበት።

አሁን ባለው አሠራር፤ ቀደም ሲል በፌዴራል መሥሪያቤቶች ብቻ ይፈጸሙ የነበሩ አሠራሮች ቀርተው አገልግሎቱ በክልሎችም የሚፈጸምበት አሠራር ተፈጥሯል። በጣም ጥቂት ካልሆነ በስተቀር ጉዳያቸው በያሉበት አካባቢ ያልቅላቸዋል። ስለዚህም ወደ ሕገወጥ ደላላ የሚያስኬዳቸው ነገር የለም።

አዲስ ዘመን፡- ታዲያ ዜጎች ጉዞአቸውን ሕጋዊ ሆነው መፈጸም እየቻሉ ከፍተኛ ገንዘብ አውጥተውና ተንገላትተው ሕገወጥ ሆነው ስመጓዝ የሚመርጡት ስምንድነው? በመንግሥት በኩል ያልተሠራ ሥራ ይኖር ይሆን?

አቶ ደረጀ፡- ሕጋዊ ሆነው መሄዳቸው ጥቅሙ ሰፊ ነው። ለጉዞ ከሚያወጡት ወጪ ጀምሮ ባለው ሂደት ውስጥ የሚገጥማቸው ችግር አይኖርም። ቅጥር ፈጽመው ለመሄድ ሲዘጋጁም ደመወዛቸውንና ሌሎች ጥቅማጥቅሞቻቸውን ቀድመው ያውቃሉ። ውልም ይገባሉ። የሠሩበትንም የሚከለክላቸው አካል አይኖርም። አሠሪያቸው ቢከለክላቸው እንኳን ከመሄዳቸው በፊት ዋስትና የገባላቸው አካል ወይንም ኤጀንሲ ስላለ ከዋስትናው ላይ ሊከፍል ይገደዳል። የማስፈጸም ኃላፊነትም አለበት።

ሠራተኛው የመብት ጥሰት ቢደርስበት መከላከልም ሆነ፣ ጥብቅና መቆም የሚቻለው በሕጋዊ መንገድ መሄድ ሲቻል ነው። በውላቸው ላይ ግዴታቸውና መብቶቻቸው በመቀመጣቸው፤ በሕግ ማስፈጸም ይቻላል። የሚመከረውም ሕጋዊ መንገድን ተከትለው እንዲሄዱ ነው።

ዜጎች እነዚህን ሁሉ ጥቅማጥቅም የሚያስገኙላቸውን ሕግ ትተው በሕገወጥ ለመሄድ ጥረት የሚያደርጉት በተለያዩ ምክንያቶች ነው። አንዱ ከግንዛቤ እጥረት ነው። ምክንያቱም ቀድመው የሚያገኟቸው በሕገወጥ ተግባር ላይ የተሠማሩትን በመሆኑ ሕጋዊ መንገድ መኖሩን አያውቁም። በዚህ ችግር ውስጥ የሚወድቁት በአብዛኛው በሀገሪቱ በገጠር የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው። የመገናኛ ብዙሃን ተደራሽነትና የመረጃ ክፍተት መኖር ያመጣው ችግር እንደሆነ ይታሰባል።

በችግር ውስጥ አልፈው ተሳክቶላቸው ሠርተው ለቤተሰብ አንዳንድ ነገር ማድረግ የቻሉትን እንደ ናሙና በማየት ለመሄድ መነሳሳት ሌላው ገፊ ምክንያት ነው። ከአቻ ግፊት በተጨማሪ ልጆቻቸው እንዲሄዱ የሚያነሳሱ ቤተሰቦችም አሉ። ደላሎችም የተሳሳተ መረጃ በመስጠት ከፍተኛ ሚና አላቸው። ደላሎች ተአማኒ መስሎ ለመታየት ከሚጠቀሟቸው ዘዴዎች ሕጋዊው አካሄድ ረጅም ጊዜ እንደሚወስድ እየዋሹ የማሳመን ሥራ ይሠራሉ።

ነገር ግን ሰዎች ያልተገነዘቡት ሕገወጥ አዘዋዋሪዎች የቅብብሎሽ ሥራ ስለሚሠሩ ችግሩም በዚያው ልክ የሰፋ ነው። በሕገወጥ መንገድ መሄድ እያስከተለ ያለው ችግር የብዙዎችን ቤት አንኳኩቷል። ምንም እንኳን ግንዛቤ መፍጠር ላይ ሰፊ ሥራ መሥራት ቢያስፍልግም በተጨባጭ እየታየ ያለው ችግር ብቻውን አስተማሪ ይመስለኛል።

የኢትዮጵያ ድንበር ሰፊ ነው። በየድንበሩ ሰዎች አቋርጠው ለመሄድ ይሞክራሉ።በድንበር አካባቢ ላይም ግንዛቤ ለመፍጠር ጥረት ሲደረግ በፍጹም ሃሳባቸውን ለመቀየር ፈቃደኛ አይሆኑም። የሞት አደጋ እንኳን

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

«49ኽ ሀ ለሜሀ ካሀያት ተመለኽት...

ዖዘፅ ፖ ፪ሽናካ

ሀኄሃ ዘመዘ፦ ለመዘ ሀኄሃ ዘመዘ፦ ለመዘ ሀኄሃ ዘመዘ፦ ለመዘ

ኢኮኖሚ

ኢንቨስትመንት

የንግዱ ዘርፍ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት መደረግ ዘርፈ ብዙ ፋይዳና ስጋት

ወርቅነሽ ደምሰው

በኢትዮጵያ ለበርካታ ዓመታት የንግድ ዘርፎች ከውጭ ኢንቨስትመንት ተከልለው እንዲቆዩ የሚያደርግ አሠራር ሲተገበር ቆይቷል። ይህም የተደረገው የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ከውጭ ባለሀብቶች ውድድር ጫና እንዲጠበቁ በማድረግ ሀብት እንዲያፈሩ ዕድል ለመስጠት፣ ከዓለም አቀፍ የንግድ ትስስር ሥርዓት ጋር እንዲተዋወቁና ልምድ እንዲቀስሙ እንዲሁም በውስጥ አቅም ላይ የተመሠረተ ዘላቂ ኢኮኖሚ ለመገንባት ታልሞ ነው።

ይሁንና አሠራሩ ዓላማውን ማሳካት እንዳልቻለ ተጠቁሟል። የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፤ ለውጭ ባለሀብቶች ዝግ የተደረጉት ዘርፎች ዝግ በመደረጋቸው የሚፈለገው ዓላማ ተሳክቷል ማለት አይቻልም።

ይልቁንም ዘርፎቹ ለውጭ ውድድር ያልተጋለጡ በመሆናቸው የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በሚፈለገው መጠን እና ጥራት እሴት ወደሚጨመሩ አምራች ኢንቨስትመንቶች የተሸጋገሩበት ሁኔታ በጣም ውስን መሆኑ ታይቷል። ከለላ በተሰጣቸው ዘርፎችም ሰፊ የአገልግሎት ተደራሽነት፣ የጥራት እና የብቃት ችግሮች ኢጋጥመዋል። ለሕገወጥ ድርጊት በሰፊው መጋለጣቸውም አሳሳቢ ሆኖ ቆይቷል።

በቅርቡ የሀገርን እና የሕዝብን ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አንጻር ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ብቻ ተከልለው የቆዩ የንግድ ኢንቨስትመንት መስኮችን ለውጭ ባለሀብቶች መክፈት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ባለፈው ሳምንት በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በኢንቨስትመንት ደንብ 474/2012 ላይ ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ብቻ ተከልለው የቆዩት እነዚህ የወጪ (Export trade)፣ የገቢ(import trade)፣ የጅምላ(wholesale trade)ና የቸርቻሮ((retail trade) የንግድ ሥራ ዘርፎች ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት እንዲሆኑ ተደርጓል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሀና አርአያስላሴ በመግለጫው ላይ ባለፉት ዓመታት የግል ዘርፉን ሚና በማሻሻል ተወዳዳሪ የሆነ ኢኮኖሚ ለመገንባት የኢንቨስትመንትና የንግድ ከባቢ ሁኔታን ምቹ ለማድረግ የሚያስችሉ ለውጦች መደረጋቸውን አስታውሰዋል። ከእነዚህ ዋና ዋና ተብለው ከሚጠቀሱት ለውጦች መካከል አንደኛው በኢንቨስትመንት ሕጉ ላይ የተደረገው ለውጥ መሆኑን አመልክተዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ከ2012ዓ.ም በፊት ብዙ ዘርፎች ለውጭ ባለሀብቶች ዝግ ሆነው ቆይተዋል። በ2012ዓ.ም የወጣው ኢንቨስትመንት አዋጅ ደግሞ ብዙ አዳዲስ ዘርፎችን ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት እንዲሆኑ አድርጓል። በተጨማሪም ባለፉት ዓመታት የፐራይቬታይዜሽንና ሌብራይዜሽን እርምጃዎች ተወስደዋል። ይህ የሆነበት ምክንያት ቀደም ሲል ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶችም ወይም ደግሞ ለመንግሥት ብቻ ተከልለው የቆዩትን ዘርፎች በመክፈት የተሻለ ተወዳዳሪነት ለማረጋገጥ ነው።

ተወዳዳሪነት ለሕዝቡም ሆነ ለሸማቾች የተሻለ ውጤት ያስገኛል ያሉት ኮሚሽነሯ፤ አጠቃላይ የኢንቨስትመንትና የንግድ ከባቢ ሕጉን ለማሻሻል ብዙ ርምጃዎች መወሰዳቸውን ተናግረዋል። ይህም ማሻሻያ በሀገር በቀል ኢኮኖሚው የተያዙትን እቅዶች ለማሳካት መንግሥት ከሚወስዳቸው ርምጃዎች መካከል አንዱና ወሳኙ መሆኑን አስታውቀዋል።

የኢንቨስትመንት አዋጁን ቁጥር ll80/ 2012 ተከትሎ በወጣው የኢንቨስትመንት ደንብ 474/2012 ላይ ለውጭ ባለሀብቶች የተከፈቱ እና ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ የተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች እንዳሉ ጠቅሰው፣ ከመንግሥት ጋር በቅንጅት ስለሚከናወኑ ዘርፎች መቀመጡንም አመላክተዋል።

የኢንቨስትመንት ደንብ 474/2012 ለዚህ ፖሊሲ ማሻሻያ መነሻ የሆኑት የወጪ፣ የገቢ፣ በጅምላና የቸርቻሮ የንግድ ዘርፎች ላይ የተሰጠውን ከለላ አስመልክቶ ኮሚሽነሯ ገልጸዋል። በቸርቻሮ ንግድ በአጠቃላይ የራስ ምርትን ከመሸጥና ከኤሌክትሮኒክስ ችርቻሮ ንግድ በስተቀር የተቀረው በሙሉ ለውጭ ባለሀብቶች የተፈቀደ አልነበረም ወይም ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች

በተፈቀዱ የንግድ ዘርፎች ላይ ለመሰማራት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የውጭ ባለሀብቶች የዳበረ ልምድ፣ አቅምና እውቀት እና ቴክኖሎጂ ያላቸው እንደሚሆኑ ይጠበቃል። ይህም የንግድ አሠራሩ የተሻላ እንዲሆን ያስችላል

ተከልሏል፤ በጅምላ ንግድ ደግሞ ነዳጅና ተዛማጅ ምርቶችን ማቅረብ፣ ሀገር ውስጥ የተመረተ የራስ ምርትን በጅምላ መሸጥና በኤሌክትሮኒክ የሚካሄድ የጅምላ ንግድ ከሚለው በስተቀር ሌላው በሙሉ ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለለ ሆኖ ቆይቷል ሲሉ ያብራራሉ።

በገቢ ንግድ (ኢምፖርት)እንዲሁ ከቡታጋዝና ከቢቱመን ንግድ በስተቀር ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት የተደረገ ዘርፍ አልነበረም ሲሉ አመልክተው፣ በውጭ ንግድ (ኤክስፖርት) ዘርፍም ጥሬ ቡና ፣ የቅባት እህሎች፣ ጫት ፣ ጥራጥሬ ፣ ቆዳና ሌጦ፣ የደን ውጤቶች፣ ዶሮና የጋማ ከብቶችን ከገበያ በመግዛት መሸጥ የሚሉት ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ብቻ ተከልለው የቆዩ ዘርፎች ነበሩ ብለዋል።

እንደ ኮሚሽነሯ ማብራሪያ፤ በቀደመው አሠራር እነዚህን ዘርፎች ለውጭ ባለሀብቶች መዝጋት ያስፈለገበት ዋንኛ ምክንያት ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ከለላ በማድረግ የተሻለ ሀብት በማፍራት ካፒታላቸውን ለማሳደግ እንዲችሉ ለማድረግ ነበር። ዓለም አቀፍ ገቢያውን እንዲላመዱት ለማድረግ እድል የተሰጠበት ሲሆን፣ በሂደት የካፒታል እድገታቸውን ተከትሎ አምራች ወደሆኑ እሴት ወደሚጨምሩ ወደ ማምረቻ ዘርፎች መሸጋገር እንዲችሉ ለማድረግ ነው።

ከዚህ አኳያ ባለፉት ዓመታት እንደ ሀገር የታየውን አፈጻጸም ስንመለከት በፖሊሲው ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ከለላ መደረጉ ውስን ውጤቶችን ብቻ ማስገኘቱን ነው ኮሚሽነሯ ያመለከቱት። የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ከለላውን ተጠቅመው ተጨማሪ ካፒታል በማግኘት ተጨማሪ እሴት ወዳለው ማምረት ሥራ ይሸጋገራሉ ተብሎ የተቀመጠውን የፖሊሲ ግብ ስንመለከት በእነዚህ የንግድ ዘርፎች የሚገኙ ብዙ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች አምራች ወደ ሆነው ዘርፍ ሲሸጋገሩ አልተስተዋለም ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪ እነዚህ ዘርፎች ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ብቻ ተከልለው መቆየታቸው ውድድር መገደቡንም ጠቅሰው፣ ለሕዝቡ ወይም ለሸማቹ በጥራት እና በዋጋ ተመጣጣኝ አቅዎችን ለማቅረብ ከፍተኛ ውስንነቶች እንደነበረም አመልክተዋል። በእነዚህ ዘርፎች የተሻለ ውድድር ለመፍጠር እና ለሸማቹም ለሕዝቡም የተሻለ ውጤት ለማስገኘት ያስችል ዘንድ ዘርፎቹ ለውጭ ባለሀብቶች እንዲከፈቱ ተወሰኗል ሲሉ ኮሚሽነሯ አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ሲባል ተከልለው የቆዩ በንግድ ዘርፎች ላይ የነበረውን ውጤት በመመልከት ጥናት አካሂዷል። በጥናቱም ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ እና ከፕላን እና ልማት ሚኒስቴር የተውጣጡ ከፍተኛ ባለሙያዎች ተሳትፈዋል፤ ጥናቱንም ለአንድ ዓመት ያህል አካሂደዋል።

በጥናቱም እስካሁን ያለው አጠቃላይ መርህ እና የንግድ ሕግ እንዴት መተዳደር አለበት የሚለው ታይቷል፤ እንደ ኢትዮጵያ ቀስ በቀስ ንግዳቸውን ለውጭ ባለሀብቶች የከፈቱ የሌሎች ሀገራትን (ቻይና፣ ህንድ ፣ ኬንያ እና ዩጋንዳና ቤትናም) ተሞክሮ በመውሰድ በአራቱም ዘርፎች ላይ ጥናት ተደርጓል። ከባለድርሻ አካላት ጋርም ውይይት ተካሂዷል። በዚህ ላይ በመመስረት የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ቦርድ ዘርፎቹ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት እንዲደረጉ ውሳኔ አስተላልፏል።

ኮሚሽነሯ፤ የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች ምንድናቸው? ለዚህ ውሳኔ ያደረሰንስ ምንድነው? የሚሉትን አጠቃላይ ሁኔታዎች አሉታዊና አወንታዊ ጎናቸው ከታየ በኋላ ጠቀሜታው ጎልቶ መታየቱንም አስታውቀዋል። የንግድ ዘርፎቹ መክፍቱ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው ጠቅሰው፣ የተሻለ አዎንታዊ ውጤት እንደሚያስገኝ አመላክተዋል።

ኮሚሽነሯ የንግዱ ዘርፍ እስካሁን ተከልሎ የቆየ ዘርፍ በመሆኑ አሁን ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት መደረጉ በአገር ውስጥ ባለሀብቶች ላይ የተወሰነ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል ሲሉም ጠቅሰው፣ የውጭ ባለሀብቶች በእነዚህ ዘርፎች ላይ ሲገቡ በርካታ ጠቀሜታዎች እንደሚኖሩም ተናግረዋል። የንግድ ሥርዓቱምን ለማዘመን በጣም ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ጠቅሰው፣ አጠቃላይ ውጤቱ ሲታይ አዎንታዊ ሚናው ያመዝናል ብለዋል ።

በሌላ በኩል በዘርፍ ላይ የሚሰማሩት የውጭ ባለሀብቶች በዘርፉ ሰፊ ልምድ ያላቸው እንደሚሆኑ ይጠበቃል ሲልም ገልጸው፣ እቃዎች ለሚያቀርቡ አቅራቢዎች የተሻለ ሁኔታ እንደሚፈጠርም ጠቁመዋል። ከእነዚህ ተቋማት ለሚገዙ ለሸማቶችም ቢሆን በጣም የተሻሉ አቅርቦቶችን የሚያገኙበት እንደሚሆን ነው ያስታወቁት።

እሳቸው እንደገለጹት፤ የንግድ ዘርፎቹ ለውጭ ባለሀብቶች መከፈት ሌሎች ፋይዳዎችም ይኖሩታል። በሸቀጦች ዋጋ ላይ የመቀነስ ሁኔታ ይፈጥራል ተብሎ ይጠበቃል። በመንግሥት ገቢም ላይ እንዲሁ አወንታዊ ውጤት ይኖራል።

ዘርፎቹ ሲከፈቱም ለእያንዳንዱ ዘርፍ የተቀመጡ ዝርዝር ቅድመ ሁኔታዎች እንዳሉም የጠቆሙት ኮሚሽነሯ፤ የውጭ ባለሀብቱ በዘርፎቹ ላይ ለመሰማራት ሊያሟላ የሚገባው ቅድመ ሁኔታ በዝርዝር መቀመጡንና ተፈጻሚ እንደሚረግም ተናግረዋል።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታው እንዳለው መኮንን በበኩላቸው፤ ተከልለው የቆዩት ዘርፎች መፈቀዳቸው በሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የተለየ ጫናን አይፈጥርም ይላሉ። በተለይ በቅድመ ሁኔታዎች በዝርዝር የተቀመጡበትና በጣም የተገደቡ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ልምድ ያለውና ቅድመ ሁኔታዎቹን ሊያሟላ የሚችል የውጭ ባለሀብት ብቻ ነው ወደ ዘርፉ ሊገባ የሚችለው ብለዋል። ይህ ደግሞ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን ከገበያ እንደማያስወጣ ተናግረው፣ ሀገሪቷ የሚያስፈልጋትን አቅርቦት ለመጨመር ታሳቢ ያደረገ መሆኑን አብራርተዋል።

በገቢ ንግድ ከማዳበሪያና ነዳጅ ንግድ በስተቀር የውጭ ባለሀብቶች በሁሉም የገቢ ንግድ ኢንቨስትመንት ላይ መሰማራት እንደሚችሉ ጠቅሰው፣ የንግድ ዘርፎቹ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት መደረጋቸው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያስገኛል ሲሉ አስገንዝበዋል።

የመንግሥት ዋና ፍላጎት እነዚህ የውጭ ባለሀብቶች በአራቱም ዘርፎች ተሰማርተው ገቢያውን እንዲለምዱ እና በሂደት ደግሞ ገቢ የሚደረጉ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ማምረት እንዲችሉ እድል እንደሚፈጥር ያመላክታሉ። እነዚህን ምርቶች በሀገር ውስጥ ሲያመርቱም የሥራ እድል መፍጠር እንደሚችሉ፣ ከሀገር ውስጥ ፍጆታ አልፈው ለውጭ ገቢያ የሚሆን ምርት እንዲያመርቱ ይደረጋል ሲሉ ሚኒስትር ዴኤታው አብራርተዋል።

የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ መምህርና የምጣኔ ሀብት ባለሙያ ዶክተር ሞላ አለማየሁ እንደሚሉትም፤ መንግሥት ዝግ ሆነው የቆዩትን ዘርፎች ለውጭ ባለሀብቶች መፈቀዱ ብዙ ጠቀሜታዎች ሊያስገኝ ይችላል። በተፈቀዱ የንግድ ዘርፎች ላይ ለመሰማራት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የውጭ ባለሀብቶች የዳበረ ልምድ፣ አቅምና እውቀት እና ቴክኖሎጂ ያላቸው እንደሚሆኑ ይጠበቃል። ይህም የንግድ አሠራሩ የተቀላጠፈና የተሻለ አሠራር እንዲከተል ያስችላል። የተሻለ የአገልግሎት ፍሰት እንዲኖር ያደርጋል። ባለሀብቶቹ ይዘውት እንደሚመጡ የሚጠበቀው እውቀትና ቴክኖሎጂም ለእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። የሥራ እድል ለመፍጠር ያስችላል።

በእነዚህ ዘርፎች ላይ የውጭ ባለሀብቶች እንዲሰማሩ ማድረግ ከሚያስገኘው ጠቀሜታ አንጻር ለኢኮኖሚ አወንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል የሚሉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፤ በጥንቃቄ ከተሠራ ደግሞ ሕዝቡ ወይም ሸማቹ የተሻለ አገልግሎት እንዲያገኝ ያስችላል ይላሉ።

ዶክተር ሞላ የንግድ ዘርፉ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት መደረጉ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችልም አመልክተዋል። የውጭ ባለሀብቶች ያፈሩትን ሀብት ወደ ሀገራቸው ሲልኩ ካፒታል ወደ ውጭ እንዲወጣ በር ይከፍታል ሲሉ ይጠቁማሉ። ለዚህም መንግሥት ጠንከር ያለ ሕግ ሊኖረው ይገባል ይላሉ። ምን ያህል መቶኛ ካፒታል መውጣት እንደሚቻል የሚያሳይ ግልጽ ሕግ ማስቀመጥ እንዳለበትም ያመለክታሉ። ይህ ካልሆነ ግን ያፈሩትን ሀብት በሙሉ ወደ ሀገራቸው ሊወስዱ እንደሚችሉም ይጠቁማሉ፤ ይህ ሁኔታ በሀገሪቱ የገንዘብ እጥረት እንዲያጋጥም እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ችግሮችም ሊፈጥር ይችላል ሲሉ ስጋታቸውን አመልክተዋል።

በሌላ በኩል ሀገር በቀል የሆኑ በማደግ ላይ ያሉ ድርጅቶች እንዲዳከሙ ወይም ከሥራ ውጪ እንዲሆኑ ያደርጋል ሲሉ ዶክተር ሞላ ያስገነዝባሉ። እነዚህ ሀገር በቀል ድርጅቶች የዳበረ ልምድ፣ እውቀትና ቴክኖሎጂ ይዘው ከሚመጡ የውጭ ባለሀብቶች ጋር መወዳደር ስለማይችሉ ከስራ ውጪ የመሆን እድላቸውም ሰፊ ይሆናል ሲሉም ይናገራሉ።

ይህ ሁኔታ ለውጭ ባለሀብቶቹ ኢኮኖሚውን የመቆጣጠር ሰፊ እድል እንደሚፈጥርላቸውና ሀገሪቱንም ትልቅ አደጋ ላይ ሊጥል እንደሚችል ያመለክታሉ። ለዚህም የተለያዩ ሀገራትን ልምድ መመልከት እንደሚቻል የሚጠቁሙት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፤ ታይላንድና ኢንዶኒዥያ ከዚህ በተያያዘ የገጠማቸውን ችግር በአብነት ያነሳሉ።

በእነዚህ ሀገራት የውጭ ባለሀብቶች ከገቡ በኋላ የፋይናንስ ዘርፉን እና የገቢና የውጭ ንግዱን በቀጥታ በመቆጣጠር ሲሠሩ ቆይተው ከሀገራቱ መንግሥታት ጋር በተከሰተው አለመግባባት ሀገሮቹን ጥለው ሲወጡ የውጭ ባለሀብቶቹን በር ከፍተው ያስተናገዱት ሀገሮች ወደ ቀድሞ ማንነታቸው ስለመመለሳቸው ታሪክቸው እንደሚያስረዳ አብራርተዋል።

እነዚህ ባለሀብቶች የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ከተቆጣጠሩ በኋላ በረጅም ጊዜ ሂደት የመንግሥት አስተዳደር እነሱን ያማከለ እንዲሆን እስከ መፈለግ የሚደርሱበት ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችል አመልክተው፣ ይህ ካልሆነ ደግሞ ከሀገር ሊወጡ ይችላሉ ሲሉ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አስታውቀዋል፤ እነዚህን ባለሀብቶች አስገድዶ ማስቀረት እንደማይቻልም ጠቅሰዋል። ለዚህም መንግሥት የሌሎች ሀገራትን ተሞክሮ በመውሰድ ሀገር በቀል ድርጅቶች በማይዳከሙበት ወይም ከሥራ ውጭ ሊሆኑ በማይችሉበት ሁኔታ ከውጭ ባለሀብቶች ጋር ጎን ለጎን ለመጓዝ የሚያስችላቸው ስትራቴጂ ነድፎ መንቀሳቀስ ይኖርበታል ሲሉ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አመልክተዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ የውጭ ባለሀብቶች ሲገቡ ከሀገር በቀል ድርጅቶች ጋር የውድድር ስሜት መፍጠር ብቻ ሳይሆን የትብብር ስሜት እንዲኖራቸው ማድረግ ላይም መሠራት ይኖርበታል፤ በሁለቱም በኩል የተሻለ እንቅስቃሴ እንዲኖር የሚያደርጉ ሕጎችና ስትራቴጂዎች እንዲኖሩ ማድረግም ይገባል።

የቁጥጥር ሥርዓቱን ጠንካራ ማድረግ የሚያስችሉ ሕጎች ፣ ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎች ማውጣት ላይ መሥራት እንደሚገባም ጠቁመዋል። ይህ ውሳኔ በሌሎች ሀገራት ላይ ተግባራዊ ተደርጎ ያስከተለው አይነት ከስተት እንዳይታይ አስቀድሞ እጅግ ጥንቃቄ የሚፈልግ እንቅስቃሴ ማድረግ ያስፈልጋል የሚል እምነት እንዳላቸው ተናግረዋል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

ጎጣዬ

እኛስ የቱጋ ነን?

ምሕረት ሞገስ

ከፅንፍ ረጋጮቹ ተርታ መሰለፍ እንደማይፈልጉ ደጋግመው የሚገልፁት ተሰማ መንግሥቴ፣ ጉበረየስ ጉበረ ማሪያም እና ዘውዴ መታፈሪያ ጠርሙስ እያጋጩ ይከራከራሉ። ፅንፈኛ መባልን ሁሉም እንደማይፈልጉ ቢገልፁም፤ በተቃራኒው በንግግራቸው ውስጥ ፅንፍ ሲረግጡ ማስተዋል አያዳግትም። በተለይ በዕለህ ሲናገሩ ፅንፈኛ መሆናቸው ያስታውቃል። የዘውዴ ደግሞ የተለየ ነው። ደጋግሞ ፅንፈኝነትን እንደሚቃወም ቢናገርም፤ በተግባር ግን ፅንፈኛ መሆኑን የሚያሳዩ ምልክቶችን ማንም በሚያውቀው መልኩ ያመለክታል።

በተደጋጋሚ የሰዎችን አመጣጥ እና አጠቃላይ የኢትዮጵያን ታሪክ ሲናገር፤ የራሱ ወገን ሀገር እንዳፀና ደጋግሞ ይገልፃል። ስለዚህ የኢትዮጵያ መስራች እና የሀገሪቱ ዋልታ የእርሱ ሰዎች ብቻ መሆናቸውን ያስረዳል። «ትክክል አይደለህም» ብሎ የሚናገረው ካለ፤ ሃሳባቸውን ለማጣጣል እና ሰዎቹ በሚሰነዝሩት ሃሳብ ለማሸማቀቅ የማያደርገው ጥረት የለም።

የሃሳብ ልዩነትን ከመቀበል እና ከማክበር ይልቅ መራር ወቀሳዎችን ከመሰንዘር ወደ ኋላ አይልም። የግለሰቦችን ሃሳብ የመስጠት ፍላጎት ከመዝጋት አልፎ ሲለው ለማስፈራራት ይሞክራል። አለማዳመጥ ብቻ ሳይሆን ያፈጠጠውን እውነት ለማየት አይፈቅድም። ጉበረየስ ለዘውዴ በተደጋጋሚ ይህ አካሒድ እንደማያዋጣው ቢነግረውም ለማዳመጥ ፈቃደኛ አይደለም።

ጉበረየስ፤ «እኔ ለዓመታት ከለፋሁለት እና ብዙ ዋጋ ከከፈልኩበት ከድርጅቴ የወጣሁበት ዋነኛ ምክንያት አቋም ስላልነበረኝ አይደለም። በድርጅቴ ውስጥ ያሉ ሰዎች ፅንፈኛ እና የራሳቸውን ጥቅም ብቻ አሳዳጅ እንዲሁም እነርሱ ከሚሉት ውጪ ሌሎችን የማያዳምጡ ሆነው በማግኘቴ ነው። ተዉ ስል የሚሰማኝ በማጣቴ ብቻ ነው። በተቃራኒው እውነትን በመያዜ ለመገለል። በመጨረሻ ያልኩት አልቀረም፤ እነርሱ ገንዘብን በማምለክ እና ሕዝብን በመርሳታቸው ዋጋ ከፈሉ።

ቁስ የሰው ልጆች መገልገያ እንጂ የሚመለክ የህልውና ጉዳይ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። ከቁስ በላይ ሰው ይቀድማል። ብዬ ብነግራቸውም ሊሰሙኝ አልቻሉም። በመጨረሻ አፍ እንጂ ጆሮ የሌላቸው መሆኑን ደጋግሞ ሲናገር የነበረው ሕዝብ አንቅሮ ተፋቸው።›› ብሎ ሊቀጥል ሲል ተሰማ አቋረጠው።

ተሰማ፤ « ቁስ አያስፈልግም ብሎ መጨፈን አያዋጣም። ምክንያቱም የሰው ልጅ በቁስ መጠቀሙ ሕይወቱን በተሻለ መልኩ እንዲኖር የሚያስችለው መሣሪያ ነው።›› አለው። ጉበረየስ «ቁስ አያስፈልግም አላልኩም። ነገር ግን ከቁስ ሰው ይበልጣል። ሁለቱም ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ናቸው። አንዱን ጥሎ ሌላውን አንጠልጥሎ መሔድ አያዋጣም። በተለይ ከሰው በላይ ቁስ ሲመለክ ውጤቱ አደገኛ ይሆናል።›› አለ።

ተሰማ ጉበረየስ የተናገረውን በቅጡ የሰማ አይመስልም፤ «ሰው ሲሠራ ለቁስ ትኩረት አትስጡ ብሎ ማጣጣል ተገቢ አይደለም። ቢያንስ ካለመሥራት መሥራት ይሻላል። እናንተ ግን በተቃራኒው ሰው ሲሠራ በርቱ እያላችሁ ከማነሳሳት ይልቅ የሚታያችሁ ከፍተቱ ብቻ ነው።›› አለ።

ጉበረየስ ከት ብሎ ሳቀ፤ « አንተም ከእርሱ የተለየህ አይደለህም። እያንዳንዱ አካሒድ ሊተች እና ሊወቀስ አይገባም ማለት ትክክል አይደለም። ተተችቶ ቢታረም ነውር የለውም። በየጊዜው የሚያጋጥሙ ትችቶች ተስፋ ሊያስቆርጡ አይገባም። በሌላ በኩል ከቁስ ጋር ልዩ ፍቅር ውስጥ መገባትም የለበትም። ምክንያቱም ቁስ ያረጃል፤ የፈጣሪ ልዩ ፍጥረት የሰው ልጅ ግን ቢያረጅም ትቶት እና ተክቶት የሚያልፈው ብዙ ነገር አለ። ለቁስ ሲሉ ሰው መጉዳት አይገባም። የሰው ልጅ ጉዳት ጠባሳው የሚሻገር ነው። ከቁስ በላይ ስለሰው ሕይወት መስራት ቀዳሚ ጉዳይ መሆን አለበት። » ሲል ተናገረ።

ተሰማ ፤« እኔ ማንም ምንም መናገር የለበትም አላልኩም። ትችት ሲኖር በልኩ መሆን አለበት የሚል እምነት አለኝ። በሚሠራው ሥራ መደሰት እና ማድነቅ ቢያቅተንም ስንተችም በጥንቃቄ ሊሆን ይገባል ባይ ነኝ። ዘውዴ ግን እንደምታየው በተደጋጋሚ የእርሱን አቋም የማይደግፉ ሰዎችን በፅኑ ይቃወማል። የሚናገሩትን ለመስማት ፈፅሞ ዕድል አይጣቸውም። በተደጋጋሚ ሃሳቡ ከኢኮኖሚ ጋር የተሳሰረ ቢመስልም እያነሳ የሚጥላቸው አጀንዳዎች መደምደሚያዎቹ ፅንፍ የወጡ ናቸው። ለምሳሌ ኑሮ ተወዷል፤ ሲል መነሻ ምክንያት የሚያደርገው የሆነ ቡድንን ብቻ ነው። ሁሉንም ጥፋት ሰብስቦ ለአንድ ቡድን ሲሰጥ፤ ‹ትክክል ነህ› ከሚለው ሰው ውጪ ሌሎችን ማዳመጥ አይፈልግም።

አንድ ሰው ከእርሱ ጋር ያለውን የሃሳብ ልዩነት ለማሳወቅ አለሳልሶ ‹በእርግጥ አንተ ተጠያቂ ያደረግከው ቡድን ክፍተቶች አሉበት፤ ነገር ግን ኑሮ እየተወደደ ያለው በኢትዮጵያ ወይም በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ሀገር እና በሁሉም ከተማዎች ነው። ይህ የሆነው ዓለም አቀፍ ችግሮች ተደራርበው በመምጣታቸው ነው።» ብሎ ሊያስረዳው ቢሞክር ለመስማት ፈቃደኛ አይደለም።

በሰዎች ግላዊ ግንኙነት ላይ ሳይቀር ለሚሰጠው አስተያየት ዘውዴ የእርሱን አቋም የሚወስድ ከሌለ ፍፁም ይነቅፋል። ሕግ ከተነሳ ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው ቢባልም በተግባር እኩል አይደሉም ብሎ ሲናገር ተቃዋሚ እና የሆነ አሳማኝ ምክንያት አቅራቢ እንኳ ቢመጣ ለመቀበል ፍላጎት የለውም።›› በማለት ተሰማ ዘውዴ ፅንፈኛ እንደሆነ እና የሰዎችን ሃሳብም ሆነ አቋም ለመስማት እንደማይፈልግ አልፎ ተርፎ ወደ ጥላቻ እንደሚያዘነብል ሲናገር ዘውዴ በመከፋት እና በትዝብት ተሰማን አየው።

ጉበረየስ በበኩሉ፤ « ሁላታችሁም የተለያያችሁ ናቸው። ተሰማ ሀገራችን ልታድግ እና ልትበለፅግ ነው ብለህ በትልቅ የተስፋ ባህር ውስጥ በደስታ ስትዋኝ፤ ከዚህ በኋላ ችግር አይኖርም የሚል ፅኑ እምነት እንዳለህ በማስተጋባት ሁሉም ያንን መቀበል እንዳለበት ታስተጋባለህ። ዘውዴ ደግሞ በተቃራኒው በአንድ ለሊት ሀገር ልትፈርስ ነው ብለህ ታስባለህ። አንተ እንዳሰብከው እና እንደተናገርከው ቢሆን ኖሮ ገና ድሮ ሀገር ፈርሳ ነበር። ነገር ግን ሀገር ትፈርሳለች ብለው ከሚያስቡት በላይ ሀገራችን ትልቅ ተስፋ አላት። ሀገራችን በፍፁም አትፈርስም የሚሉት ስለበዙ ሀገራችን አሁንም አለች። ይህ የእኔ እምነት ነው።

በእኔ በኩል በተደጋጋሚ እኔ እንዳለሁ፤ ቤተሰቦቼ ያልቃሉ፤ ሀገር ትፈርሳለች ከማለት ይልቅ እንዳልጎዳ እና ቤተሰቦቼ እንዳያልቁ ሀገሬ እንዳትፈርስ ምን ላድርግ ብሎ ማሰብ እና ያንንም ግዴታ መወጣት እንዲሁም የሚጠበቅብህን መሥራት ይሻላል። ፍፁም ጽፅልመት ምንም መፍትሔ አያመጣም፤ መጨረሻው በተመሳሳይ መልኩ ያው ጽልመት ነው። የሚሻለው ከጽልመት ወደ ብርሃን መምጣት ነው። ራስን ማየት መገምገም እና ማረም፤ ፍፁም መስመር ከለቀቀ ፅንፈኝነት ወደ መካከለኛው መንገድ መምጣት ያስፈልጋል።›› አለ።

ተሰማ በበኩሉ እርሱ ሳይሆን ፅንፈኛው ዘውዴ እንደሆነ ለማስረዳት፤ «ኢትዮጵያ በማደግ ላይ ያለች ሀገር እንደሆነች እየታወቀ ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ይሆናል ብሎ መጠበቅ የዓለምን ተጨባጭ ሁኔታ ካለመረዳት የመነጨ ይመስለኛል። ዘውዴ ይህንን አይገነዘብም ትንሽ ትችት ሲነሳ ያዙኝ ልቀቁኝ ይላል። ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ እንደሆነ ሁሉም ሰው እንዲያስብ ይፈልጋል። ይህ ደግሞ እንኳን ኢትዮጵያን በመሰለ ሀገር ቀርቶ አደጉ በሚባሉት ሀገራት እንኳን የሚታሰብ አይደለም።

ሁልጊዜም ከጥሩ ሥራዎች ጎን ለጎን የሚተቹ፤ የሚታረሙና የሚወቀሱ ሥራዎች ሊኖሩ ይገባል። ሀገርም የምታድገው ጎሽ፤ ጎሽ በሚሉ ሃሳቦች ሳይሆን የሰላ ትችት በሚያቀርቡ ዜጎች ጭምር ነው። ስለዚህም አድናቆት ብቻ ሳይሆንም ትችትንም አጥብቆ መሻት አለብን። ›› አለ።

ዘውዴ ሁለቱም በየተራ ሲወርዱበት ምላሽ አልሰጠም። የተናገረው፤ «እንደፈለጋችሁ ማለት ትችላላችሁ። እኔ ያልኩት መሸፋፈን ይቅር ነው። ነገሮችን በመሸፋፈን ቁጥር ለመፍትሄውም እየራቅን እንመጣለን። ደግሞ ብዙዎቹ የምንሸፋፍናቸው ነገሮች ሳይውል ሳያድር መታወቃቸው አይቀርም። ቢታወቁ እንኳን ችግር የሚያመጡ አይደሉም።

የመሸፋፈን አባዜ ስለተጠናወተን የማይሸፈነውን ሁሉ ለመሸፋፈን እንሞክራለን። ይህ ሲሆን ደግሞ ነገሩ ከአቅሙ በላይ ግዝፈት አግኝቶ የሰው ቀልብ ይስባል። እውነታው ሲገለጥ ግን የሸፈንነው ጉዳይ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ስለዚህም ሁላችንም የመፍትሄው አካል እንድንሆን ነገሮችን በግልጽ አውጥተን እንወያይባቸው። ይህን ተገንዝቦ እኮ መንግሥት በግልጽ እንወያይ፤ እንመካከር እያለ ነው። የምክክር ኮሚሽን አቋቁሞ የደባበቅናቸውን ሃሳቦች በሙሉ በግልጽ እንነጋገርባቸውና መፍትሄ እናስቀምጥላቸው እያለ ነው። በግልጽ ስንወያይ፤ ስንመካከረው ነው መፍትሄ ላይ የምንደርሰው የሚል ጽኑ እምነት አለኝ።

የኢትዮጵያ ችግር ለዘመናት ሳይፈታ እዚህ የደረሰው መነጋገር ባለመቻላችን ነው። ዝምታን መርጠን ፤መወያየትን ፈርተን ፤ ተደባብቀን በመኖራችን አሁንም ችግራችንን ታቀፈን ይዘናል። ስለዚህም ማለባበስ ይቅር ነው ያልኩት ›› ብሎ ሃሳቡን ቋጨ።

ጉበረየስ በበኩሉ፤ «እኔ አትተች አላልኩም። መተቻቸት ሃሳብን በሃሳብ መቃወም አስፈላጊ ነው። ያለበለዚያ ሰዎች ከስህተታቸው ሳይታረሙ እዛው በተቸከሉበት ይቆማሉ። ቆሞ መቅረት ደግሞ ፍሬ አያስገኝም። የማያዳምጥ እርሱም ቆይቶ አዳማጭ ማጣቱ የማይቀር ነው። የሚያዳምጥ ይማራል፤ እርሱም ተደማጭ ይሆናል። አሁን በዋናነት የሚያስፈልገው ተደጋጋሚ ትችት እና ወቀሳ አይደለም። ይህ ሲባል አትተቹ ለማለትም አይደለም። ገንቢ ትችት ቦታ ሊሰጠው ይገባል። በዋናነት ግን ማንም ቢሆን ራሱን ለመተቸት ማዘጋጀት አለበት። የሚሠራ ቢተች ችግር የለውም። ራሱን ያሻሽላል። የማይሰራም ሥራው መተቸት ብቻ ሊሆን አይገባም። ደግሞ በወቀሳና በምክክር መካከል ያለውን ልዩነት መርሳት አይገባም።

ሁሉም ሥራውን መሥራት እና ግዴታውን መወጣት አለበት። መታረምም የትልቅነት መገለጫ ነው። ሰው አብሮ ሲኖር መጋጨቱ አይቀርም። ወይም በመኖርም ሆነ በመምራት ሂደት አንድ ሰው ከስህተት የፀዳ አይሆንም። ማንም ሆነ ማን ሊያጠፋ ይችላል። እንኳን የሚመራ እና የሚሠራ አብሮ እየበላ የሚኖር አንድ ቤተሰብም እርስ በራሱ የማያስማሙት ነገሮች ሊጋጥሙት ይችላሉ። ለዚህ መፍትሔው አንዱ ሌላውን ማዳመጥ እና ራሱን በዛ ሰው ቦታ ላይ ተክቶ ማየት ያስፈልጋል። ዋናው ጉዳይ ማንም መጎዳት የለበትም። ሁሉም አንድ ወገንን ለመጥቀም እና አንዱን ወገን የበላይ ለማድረግ ሳይሆን ኢትዮጵያን ከፍ ለማድረግ ይሥራ፤ ይህ እንዲሆን የእውነት ምክክር ያስፈልጋል። ይሄንን ከልቤ እቀበላለሁ።

ምክክር የሁሉም ነገር መፍትሄ እንደሆነ ማመን ይገባናል። አንዳንዶቹ እኮ እንመካከር ሲባል እንታኮስ የሚሉ ናቸው። በጠረጴዛ ዙርያ እንወያይ ሲባሉ በጥይት እንፈታተሽ የሚሉ በርከተዋል። የሀገር ፍቅርና ከብር ተዘንግቷቸው ብሄር አምላኪ ሆነው ብሄሬ ተነካ በሚል ሽፋን ጦር የሚመዙ መብዛታቸው ሁላችንም እየኖርንበት ያለው ሀቅ ነው።

እናም ጽንፈኛ ሆነን ስንገኝ በተዘዋዋሪ እነዚህን ሰዎች ሃሳብ መደገፋችን መሆኑን ማስተዋል አለብን። ከየትኛው አካባቢ ይምጣ የጽንፈኛ አስተሳሰብ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም። የአንዱ ቅዱስ የሌላው ርኩስ የሚሆንበት ኢጋጣሚ አይኖርም። ካወገዝንም ፤ ከደገፍን አንድ መሠረት ላይ ቆመን ሊሆን ይገባል። ይህ መሠረታችን ደግሞ ኢትዮጵያዊነት ነው። ኢትዮጵያ የሚጎዳ በሙሉ ከየትም ይምጣ ሊወገዝ ይገባል። ኢትዮጵያን የሚጠቅም ከሆነ ደግሞ ማንም ይናገር ፤ ማንም ይሥራው ሁላችንም በደስታ ልንቀበለው ይገባል። ጽንፍ ላይ ቆመን የምንደግፈውም ሆነ የምንቃወመው ነገር ውጤቱ እኩል ነው። ከጽንፈኛ አስተሳሰብ የሚወጣ መልካም ቃላትም ሆነ ድርጊት የለም። ሁሉም ጎጂ ነው። በማለት ጉበረየስ ሁለቱንም ፈገግ ብሎ አያቸው። ተሰማ ገራገር በመሰለ ፊቱ ፈገግ አለ። ዘውዴ ግን ግንባሩን እንደቋጠረ « ወይ መሬት ያለ ሰው?›› ብሎ ከመቀመጫው ተነሳ።

ትችት ሲኖር በልኩ መሆን አለበት የሚል እምነት አለኝ። በሚሠራው ሥራ መደሰት እና ማድነቅ ቢያቅተንም ስንተችም በጥንቃቄ ሊሆን ይገባል ባይ ነኝ

ԱՍՏՎԱԾԱՀԱՅՏՈՒԹՅՈՒՆ

ՀԱՅԿԱԿԱՆ ՀԱՄԱՅՆՔՆԵՐԻ ՄԱՍԻՆ

Հայկական համայնքներ

ማህበራዊ

ልዩ ልዩ

የትምህርት ዕድል ከኦቲዝም ጋር ለሚኖሩ

አየሩስ ተስፋዬ

አቶ ዘሪሁን ተከስተ ከኦቲዝም ጋር የሚኖር ልጅ አላቸው። ልጃቸው ይህ ሕመም እንዳለበት ሲያውቁ ነበር ትምህርቱን እንዲከታተል ወደ ጆይ የኦቲዝም ማዕከል የላኩት። ልጃቸው ወደ ማዕከሉ ካቀና በኋላ ብዙ ነገሮችን አውቋል። ለዚህም እርሳቸው ምስክር ናቸው።

ደመቀች ታደለ ደግሞ የአስራ አንድ ዓመት ልጇ የአዕምሮ እድገት ውስንት አለበት። ያለማንም ድጋፍ በብዙ ፈተና እያሳደገቸው ትገኛለች። ልጇን ወደ ትምህርት ቤት ለመላክ የብዙ ትምህርት ቤት ደጆችን ረግጣለች። በደስታ ግን አልተቀበሏትም ነበር። ልጇም ዕድሜው ለትምህርት በደረሰበት ሰዓት አልነበረም ወደ ትምህርት ቤት ያቀናው። አስር ዓመታትን ከእናቱ ጉያ ውስጥ ሆኖ ያሳለፈው ብዙ ምክንያቶች አስገድደውት ነው። በግዜው እርሷ አቅም ስላልነበራት እንዲህ አይነቱ ሕመም ያለባቸውን ልጆች ወደሚያግዙ ማዕከላት ለማስገባት አልታደለችም። ሆኖም ከብዙ ፈተናና ደጅ ጥናት በኋላ ልጇ ትምህርት ቤት ገብቶላታል።

በሁለቱ ወላጆች መካከል ያለው ልዩነቱ ግልጽ ነው። ብዙ አቅም የሌላቸው እንደ ደመቀች ያሉ ወላጆች ልጆቻቸውን ለማን ሰጥቼ ልውጣ ብለው በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሲፈተኑ ይስተዋላል። ለጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶ ካልተሠራበት እንደ ሀገር የሚመጣውን ቀውስ ለመረዳት አያዳግትም።

ዓሊ ሳኒ በዲላ ዩኒቨርሲቲ የልዩ ፍላጎት እና የአካቶ ትምህርት ከፍል ረዳት ፕሮፌሰር ናቸው። በ «ላይት ፎር ዘ ወርልድ» በተሰኘ ድርጅት ደግሞ የአካቶ ትምህርት አማካሪ በመሆን ያገለግላሉ። እርሳቸው እንደሚያብራሩት በኢትዮጵያ የሁሉም አካል ጉዳተኞች ተሳትፎ ቁጥር አናሳ ነው። የዓለም ባንክ ከሚያስቀምጠው ቁጥር ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ ነው ለማለት ያስደፍራል። የትምህርት ተሳትፏቸውን ሲታይ ደግሞ ቅድመ አንደኛ ላይ ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱ ተማሪዎች ቁጥር 0 ነጥብ 9 በመቶ ነው።

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ላይ 10 ነጥብ 6 ከመቶ ነው። የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር ደግሞ 3 ነጥብ 6 ከመቶ ብቻ ነው። ከኦቲዝም ጋር የሚኖሩ ልጆች ግን ምን ያህሎቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደመጡ ወይም እንደቀሩ በውል የሚያሳይ መረጃ የለም።

እንደ ረዳት ፕሮፌሰሩ ገለፃ ኦቲዝም ያላቸውን ልጆች በመንግሥት ትምህርት ቤት እንዲካተቱ ፍላጎት ቢኖርም ድጋፉ በቂ ነው አይደለም። እንደውም ከኦቲዝም ጋር ተያይዞ ጥሩ ሥራ ሠርተዋል የሚባሉት አንዳንድ ረጂ ማዕከላት ናቸው። ለአብነት እንደ «ነህምያ» የኦቲዝም ማዕከል፣ «ጆይ» የኦቲዝም ማዕከል እና ሌሎችም ይጠቅሳሉ። እነዚህ ማዕከላት በግለሰቦች ተነሳሽነት የተከፈቱ ሲሆኑ አብዛኞቹም ኦቲዝም ያላቸው ልጆች ኖሯቸው ልጆቻቸውን የት መውሰድ እንዳለባቸው ግራ ሲጋቡ በራሳቸው ተነሳሽነት ከፍተው ለሌሎች ጭምር የተረፉ ናቸው።

እነዚህ ማዕከላት ጥቂት ናቸው ብቻ ሳይሆን በአዲስ አበባ ብቻ የተወሰኑ ናቸው። በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍል አካል ጉዳተኛም ሆኑ ከኦቲዝም ጋር የሚኖሩ ልጆች ያሏቸው ወላጆች በድህነት ውስጥ ያሉ ናቸው። እነዚህ ተቋማት ደግሞ በንጽጽር በአብዛኛው በአዲስ አበባ ነው የሚገኙት። ከዚህ ጋር ተያይዞ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ወላጆች ተደራሽ እየሆኑ አይደለም።

ኦቲዝም ያላቸው ልጆች እንደማንኛውም ልጅ አካላዊ እድገት አላቸው። ነገር ግን ሃሳባቸውን የመግለጽ እና ከሌሎች ሰዎች ጋር የመቀላቀል ችግር ስላለባቸው የልጆቹን ድጋፍ ውስን እንዲሆን እና ለጉዳት እንዲጋለጡ ያደርጋቸዋል። በተለይም ሴቶች የመደፈር ዕድላቸው ሰፊ ነው። ወላጆችም ስለ ሥነ ተዋልዶ ጤና ትምህርት በግልጽ ማስተማር ይገባቸዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚመጣው ችግር ውስብስብ እንደመሆኑ መንግሥትም በቂ ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል።

ዶክተር አሊ(ዶ/ር) እንደሚያስረዱት በመንግሥት በኩል ከኦቲዝም ጋር ለሚኖሩ ልጆች በአቅራቢያቸው የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ማመቻቸት ይጠበቅበታል።

ችግሩን ለመፍታት መንግሥት መሥራት ካለበት ሥራ ጎን ለጎን ወላጆች በኦቲዝም ዙሪያ ሥልጠናዎችን መውሰድ፣ ማንበብ እና ተመሳሳይ ልጆች ካሏቸው ወላጆችን ጋር መወያየት እና መነጋገር ቢችሉ የልጆቻቸውንም ሆነ የራሳቸውን ሕይወት ማሻሻል እንደሚችሉ ያስረዳሉ

በተመሳሳይ እነሱን የሚያስተምሩ መምህራንም በየትምህርት ቤቱ መመደብ ያስፈልጋል። አስፈላጊ የትምህርት ቁሳቁሶችንም ማሟላት ይገባል። በእርግጥ ይህ ሥራ የመንግሥት ብቻ ሳይሆን የሁሉም ኃላፊነት በመሆኑ መንግሥት ከበላይ ሆኖ ሁሉንም የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር መሥራት ይጠበቅበታል።

የሦስተኛ ዲግሪ መመረቂያ ጽሑፋቸውን በልዩ ድጋፍ ላይ የሠሩት ረዳት ፕሮፌሰር አሊ ሳኒ በኦቲዝም ዙሪያ የተሠሩ ጥናቶች እንኳን በቂ እንዳልሆኑ ይናገራሉ። ኦቲዝም ያለባቸውን ልጆች የሚያሳድጉ ወላጆች ጫናን በተመለከተ በሠሩት ጥናት የወላጆች የኦኗኗር ሁኔታ እጅጉን የሚፈትን እንደሆነ ያስረዳሉ። ችግሩን ለመፍታት መንግሥት መሥራት ካለበት ሥራ ጎን ለጎን ወላጆች በኦቲዝም ዙሪያ ሥልጠናዎችን መውሰድ፣ ማንበብ እና ተመሳሳይ ልጆች ካሏቸው ወላጆችን ጋር መወያየት እና መነጋገር ቢችሉ የልጆቻቸውንም ሆነ የራሳቸውን ሕይወት ማሻሻል እንደሚችሉ ያስረዳሉ። አከለውም ልጆቻቸው ራሳቸውን ችለው ነገሮችን መከወን እስከሚችሉ ድረስ ያለመታከት መሥራት እንዳለባቸው በመግለጽ፤ ነገር ግን ወላጆች ልጇ ያለ እኔ መኖር አይችልም ወደሚል ጭንቀት መሸጋገር የለባቸውም ይላሉ።

ከኦቲዝም ጋር የሚኖሩ ልጆች አንደኛው ፈተናቸው የተግባቦት እንደመሆኑ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የንግግር ሕክምና (ስፒች ቴራፒ) ትምህርት ለመስጠት ጥረት እየተደረገ እንደሆነ የሚገለጹት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ የልዩ ፍላጎት እና አካቶ ትምህርት ባለሙያዎች መሥራት ቢችሉ ችግራቸውን ለመቀነስ ይረዳል። የአካቶ ትምህርት ሁሉም አካል ጉዳተኞች እንደ አካል ጉዳታቸው ሁኔታ አካታች የሆነ ትምህርት መስጠት ነው። ከኦቲዝም ጋር ለሚኖሩ፣ የአዕምሮ እድገት ውስንት ላለባቸው፣ ለዓይነ ስውራን እና ለሌሎች አካል ጉዳተኞች የአካቶ ትምህርት ይሰጣል። ነገር ግን ራሱን የቻለ ሥርዓተ ትምህርት (ካሪኩለም) የለውም ይላሉ።

ከዚህ ባለፈ በኢትዮጵያ የትምህርት እና ሥልጠና ፖሊሲ እንጂ የትምህርት ሕግ የለንም። አካታች እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀው የትምህርት ሕግ ረቂቁ ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ከተላከ አራት ዓመታት ባስቆጠረበት ሁኔታ ከኦቲዝም ጋር የሚኖሩ ልጆችን ወደ ትምህርት ቤት ለመላክ አስገዳጅ ሁኔታ ሊኖር እንደማይችል ያስረዳሉ። ከዚህ ይልቅ ኦቲዝም ሆነ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸውን ልጆች ትምህርት ቤት ለማስገባት በማባበል፣ በልምምጥ እና ተፅዕኖ በማሳደር ነው ልጆቹ እየተመዘገቡ ያሉት ዓሊ (ዶ/ር)፤ ይህም ተገቢ እንዳልሆነ ይገልጻሉ።

ዓለም አቀፍ

ዩክሬን በውጭ ሀገራት ለሚኖሩ ዜጎች አገልግሎት መስጠት አቆመች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ዩክሬን በውጭ ሀገራት ለሚኖሩ ዜጎች አገልግሎት መስጠት አቆመች።

ለአንድ ሳምንት ልዩ ዘመቻ በሚል የተጀመረው የሩሲያ- ዩክሬን ጦርነት ሦስተኛ ዓመቱ ላይ ይገኛል።

ይህ ጦርነት በድርድር እንዲቆም የተለያዩ ጥረቶች ቢደረጉም እስካሁን መልኩን እየቀያየረ ቀጥሏል።

ዩክሬን ባንድ በኩል የጦር መሣሪያዎችን ከተለያዩ ሀገራት በማሰባሰብ ላይ ስትሆን በሌላ በኩል ደግሞ አዲስ ወታደራዊ ግዳጅ በዜጎቿ ላይ ጥላለች።

ሀገሪቱ ከሩሲያ ጋር ለሚደረገው ጦርነት እድሜያቸው ከ18-60 ዓመት የሆናቸው ዜጎች ወታደራዊ ተቋሟን እንዲቀላቀሉ ግዳጅ ጥላለች።

ጦርነቱ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ 4 ነጥብ 3 ሚሊዮን ዩክሬናዊያን ወደ ተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት እንደተሰደዱ ተገልጿል።

ይሁንና ዩክሬን የወታደር እጥረት ማጋጠሙን ተከትሎ በውጭ ሀገራት ያሉ ዜጎቿ እንዲመለሱ እና ሀገራቸውን ከሩሲያ ጥቃት እንዲጠብቁ ጥሪ አድርጋለች።

ይሁንና እነዚህ በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ዩክሬናውያን ወደ ሀገራቸው በግዴታ እንዲመለሱ ፓስፖርት እና መሰል አገልግሎቶችን በውጭ ሀገራት ባሉ ኤምባሲዎች እና ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች እንዳያገኙ እገዳ ጥላለች።

ዩክሬን በውጭ ሀገራት ተሰደው ካሉ ዜጎቿ መካከል 860 ዩክሬናውያን እድሜያቸው 18 እና ከዛ በላይ ይሆናል ተብሏል።

እድሜያቸው የሀገሪቱን መከላከያ ሠራዊት እንዲቀላቀሉ የሚፈቅድላቸው እና በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ዩክሬናውያን ወደ ኪቭ ካልተመለሱ ማንኛውም የዜግነት አገልግሎት እንዳይሰጣቸው እገዳ እንደተጣለባቸው ሮይተርስ ዘግቧል።

ይህ በዚህ እንዳለ ሩሲያ በምሥራቃዊ ዩክሬን በኩል ድል እየቀናት እና ቦታዎችን ከዩክሬን ጦር እየተረከበች መሆኗ ተገልጿል።

የአሜሪካ ሕግ አውጭ ምክር ቤት ዩክሬንን ጨምሮ ለእስራኤል እና ታይዋን ከ60 ቢሊዮን በላይ ዶላር እርዳታ እንዲሰጥ ውሳኔ አሳልፏል።

እስራኤል የሀማስ የመጨረሻ ምሽግ ይገኝባታል የምትላትን ራፋን ለማጥቃት በቀጣይ ሳምንት ንጹሐንን ልታስወጣ ነው ተባለ

በጋዜጣው ሪፖርተር

እስራኤል የሀማስ የመጨረሻ ምሽግ ይገኝባታል የምትላትን ራፋን ለማጥቃት በቀጣይ ሳምንት ንጹሐንን ልታስወጣ ነው ተባለ።

እስራኤል የሀማስ የመጨረሻ ምሽግ ይገኝባታል የምትላትን የራፋ ከተማ ለማጥቃት በሚቀጥለው ሳምንት ንጹሐንን ማስወጣት እንደምትጀምር ተገልጿል።

እስራኤል ከራፋ ለሚወጡ ሰዎች መጠለያ የሚሆን በ10 ሺዎች የሚቆጠር ድንኳን መግዛቷን ሮይተርስ የእስራኤል ምንጮችን ጠቅሶ ዘግቧል።

በግብጽ ድንበር የምትገኘው የጋዛ ከተማ ግማሽ ዓመት በሆነው የእስራኤል እና ሀማስ ጦርነት ሸሽተው በመጡ ተፈናቃዮች ተጨናንቃለች። ይህ የእስራኤል ራፋን የማጥቃት እቅድ የስደተኛ ማዕበል ሊከሰት ይችላል የምትለውን ግብፅን እና ምዕራባውያን ስጋት ውስጥ ከቷል።

በንጹሐን ጥበቃ ጉዳይ ከአሜሪካ መንግሥት ጋር ለሳምንታት ውይይት ከተካሄደ በኋላ የእስራኤል መከላከያ ሚኒስቴር እያንዳንዳቸው ከ10-12 ሰዎች ማስጠለል የሚችሉ 40,000 ድንኳኖችን መግዛቱን ዘገባው ጠቅሷል።

በኢንተርኔት የተሰራጨ ቪዲዮ ከራፋ በአምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ካን ዮኒስ ነጭ ድንኳኖች ተደርድረው ያሳያል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ኔታንያሁ የጦር ካቢኔት ንጹሐን የማስወጣት ሥራ ለማስጀመር በሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት ውስጥ ይሰበሰባል ተብሏል።

እስራኤል በራፋ ከተማ ጥቃት እንዳታደርስ የእስራኤል እና ሀማስ አደራዳሪዎች ግብፅ፣ ኳታር እና አሜሪካ ጫና ቢያደርጉም፣ እስራኤል የማጥቃት እቅዷን አልቀለበሰችም።

እስራኤል የሀማስ የመጨረሻ ምሽጎች የሚገኙት በራፋ ስለሆነ ራፋን ማጥቃት ሀማስን ሙሉ በሙሉ ለመደምሰስ አስፈላጊ ነው ብላ ታምናለች።

ባለፈው ጥቅምት ወር ሀማስ ያደረሰውን ጥቃት ተከትሎ እስራኤል በጋዛ እየወሰደችው ባለው መጠነ ሰፊ የአየር እና የምድር ጥቃት የተገደሉ ፍልስጤማውያን ቁጥር ከ34 ሺህ በላይ አልፏል።

ስፖርት

የፕሮጀክቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና በሐዋሳ እየተካሄደ ነው

ዓለማየሁ ግዛው

2ኛው የኢትዮጵያ ታዳጊ ፕሮጀክቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና በሐዋሳ ስታዲየም እየተካሄደ ነው፡፡ ሻምፒዮናው ትናንት በሲዳማ ክልል አስተናጋጅነት መካሄድ የጀመረ ሲሆን፣ በውድድሩ ዕድሜያቸው ከ16 እና 18 ዓመት በታች የሆኑ ከአስር ክልሎችና ሁለት ከተማ አስተዳደሮች የተወጣጡ የታዳጊ ፕሮጀክት አትሌቶችን ያፎካክራል፡፡

ሻምፒዮናው በተለያዩ ውድድሮች ትናንት ሲጀመር የፍጻሜና የማጣሪያ ፉክክሮች ተካሂደዋል። ከሚያዝያ 16 እስከ 19/2016 ዓ.ም በሚካሄደው በዚህ ሻምፒዮና ትናንት ከ18 ዓመት በታች የ3 ሺ ሜትር ውድድርን ጨምሮ አራት የሜዳ ተግባራት ፉክክሮች ፍጻሜ አግኝተዋል፡፡ በርዝመት ዝላይ ሴቶች፣ በወንዶች አሎሎ ውርወራ፣ በሴቶች ጦር ውርወራ እና ዲስከስ ውርወራ ፍጻሜ ያገኙ የሜዳ ተግባራት ውድድሮች ናቸው።

በሴቶች ከ18 ዓመት በታች ዲስከስ ውርወራ የፍጻሜ ውድድር ሴና ሴሊ ከኦሮሚያ ክልል 23.49 በመወርወር የወርቅ ሜዳሊያ አጥልቃለች። በተመሳሳይ ሜቲ ረታ ከኦሮሚያ ክልል 19.70 በመወርወር የብር ሜዳሊያ እና ሜሮን ኃይሉ ከድሬዳዋ 15.94 ሜትር በመወርወር የነሐስ ሜዳሊያ ተሸልመዋል።

ከ18 ዓመት በታች ወንዶች አሎሎ ውርወራ ፊይሳ ሮቤ ከኦሮሚያ ክልል 12.86 ሜትር በመወርወር የወርቅ ሜዳሊያ ወስዷል። ዓባይነህ ሙዴ ከሲዳማ ክልል 12.08 ወርውሮ የብር ሜዳሊያ አሸናፊ ሲሆን ብሩክ ሉባሞ 11.32 ሜትር በመወርወር የነሐስ ሜዳሊያ አጥልቋል። ከ18 ዓመት በታች ሴቶች ርዝመት ዝላይ ደራርቱ ዳንኒሳ ከሲዳማ ክልል 4.78 በመዝለል 1ኛ ሆና ስታጠናቅቅ፣ መዓዛ ገረመው ከአዲስ አበባ 4.61 ሜትር በመዝለል የብር ሜዳሊያ ተሸላሚ፣ ኮኬት እምሩ ከኦሮሚያ 4.41 በመዝለል 3ኛና የነሐስ ሜዳሊያ

ሻምፒዮናው ከመጀመሪያው ቀን አንስቶ በተለያዩ ውድድሮች የፍፃሜ ፉክክሮችን አስተናግዷል፣

ተሸላሚ መሆን ችላለች።

ከ16 ዓመት በታች ሴቶች የጦር ውርወራ ሌላው ፍጻሜ ያገኘ ውድድር ሲሆን ብዙነሽ አድማሱ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ ሽቶ ባናታ ከኦሮሚያ ክልልና ቢቱ በርሶ ከኦሮሚያ ክልል ከ1ኛ እስከ 3ኛ በመውጣት የወርቅ ብርና የነሐስ ሜዳሊያ ተሸልመዋል።

የ3 ሺ ሜትር ከ18 ዓመት በታች ወንዶችና ሴቶች ውድድር ከፍተኛ ፉክክር በማስተናገድ አሸናፊዎቹ ተለይተዋል። በሴቶች መካከል በተካሄደው ፉክክር አስቴር አርኬ ከሲዳማ 9:17.87 ሰዓትን አስመዝግባ በቀዳሚነት ጨርሳለች። ጥበበ እንየው ከአዲስ አበባ 9:54 ሰዓት 2ኛ እና ህልፈይ ካሣይ ከትግራይ ክልል 9:28.37 3ኛ ደረጃን በመያዝ አጠናቀዋል፡፡ በወንዶች መካከል ከፍተኛ ፉክክር የተደረገ ሲሆን ኃይሉ አያሌው ከድሬዳዋ 1ኛ በመሆን የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ ሆናል፡፡ አማኑኤል ሀብቱ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ 2ኛና የብር ሜዳሊያ ተሸላሚ፣ ተስፋዬ ወዳይ ከኦሮሚያ 3ኛና የነሐስ ሜዳሊያ ተሸላሚ በመሆን አጠናቀዋል።

የ 800 ሜትር፣ 400 ሜትርና የ100 ሜትር ከ16 ዓመትና ከ18 ዓመት በታች የማጣሪያ ውድድሮች የተካሄዱ ሲሆን ወደ ቀጣይ ዙር ያለፉ አትሌቶች ተለይተዋል።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የተሳትፎና ውድድር ዳይሬክተር አቶ አስፋው ዳኜ የውድድሩ ዋና ዓላማ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለሚገኙ የፕሮጀክት አትሌቶች የውድድር ዕድል መፍጠር መሆኑን ተናግረዋል። የፕሮጀክቶችን የሥልጠና ሂደት በውድድር በመለካትና በመገምገም ድጋፍ ለማድረግ አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር መሆኑንም አክለዋል። በተጨማሪም ከክልልና ከተማ አስተዳደር ለሚመጡ አትሌቶች፣ አሠልጣኞችና ባለሙያዎች የእርስ በርስ የሙያና የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ይጠቅማል። ተተኪና ሀገርን በአሕጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ ውድድሮች የሚወክሉ ውጤታማ አትሌቶችን ለማፍራት የሚያግዝ የታዳጊዎች ውድድር መሆኑንም ገልጸዋል።

አቶ አስፋው የታዳጊዎች ውድድር ጥንቃቄ የሚፈልግ በመሆኑ ጠንካራ የሆነ ዝግጅት መደረጉን ገልጸው፣ አትሌቶች በውድድር ተግባራት፣ ከተወዳዳሪዎች ብቃት የአሯሯጥ ቴክኒክ ልምድን የሚቀስሙ ስለሆነ በሙያቸው ብቁ የሆኑና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሥልጠና የወሰዱ ልምድ ያላቸው ዳኞች ተመርጠው ውድድር እየተካሄደ ነው። ከምዝገባ ጀምሮ የውድድሩን ሕግና ደንብ ለሚመለከታቸው አካላት ከማድረስ ጀምሮ ሰፊ ሥራዎች ተሠርተው ወደ ውድድር መገባቱንም አስረድተዋል።

ፌዴሬሽኑ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከአበረታች መድኃኒትና ከዕድሜ ማጭበርበሮች ጋር ጥንቃቄ እንዲደረግ ቀድሞ ደብዳቤ መላኩን የገለፁት አቶ አስፋው፣ የሕክምና ቡድኑ ለየት ያሉ ቅጾችን በማዘጋጀት ክልሎችን የዕድሜ ማምገማ አሠርቶ እንዲመጡ ማድረጉን ተናግረዋል፡፡ ዕድሜ አጭበርብረው የሚገኙ አትሌቶች፣ አሠልጣኝን እና የቡድን መሪን ተጠያቂ እንደሚያደርግ ፌዴሬሽኑ አስታውቋል። ይህ እንዳይሆን የማስተማርና የማስጠንቀቅ ሥራ እየተሠራ እንደሆነም ተጠቅሷል።

የዘንድሮ ውድድር በተወዳዳሪ ብዛት የተሻለና ብዙ አትሌቶች በትክክለኛ የእድሜ ደረጃ በመምጣታቸው ይሄንን አጠንክሮ ለማስቀጠል እንደሚሠራም አቶ ዳኜ ገልጸዋል። በሕክምና ቡድኑ ለታዳጊዎች በአበረታች ቅመሞች ዙሪያ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ እየተሠራም ይገኛል። ታዳጊ አትሌቶች ንጹሕ የሆነ አዕምሮቸው ወደ ሌላ እሳቤ ሳይሸጋገር ቅድሚያ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላልም ተብሏል።

በውድድሩ ከ10 ክልሎችና ከሁለት ከተማ አስተዳደሮች የተወጣጡ ዕድሜያቸው ከ16 ዓመትና 18 በታች የሆኑ 203 ሴትና 247 ወንድ በአጠቃላይ 450 አትሌቶች ይሳተፋሉ። ውድድሩ ዛሬ፣ ነገና ከነገ በስቲያ ቀጥሎ የሚካሄድ ሲሆን የተለያዩ የማጣሪያና የፍጻሜ ውድድሮችም ይጠበቃሉ።

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለስልጣን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

ለመዲናዋ መዘመን- የተቋማት ቅንጅታዊ አሠራር

ስሜነህ ደስታ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን እንደገና በአዲስ መልክ ከተቋቋመ ጀምሮ በርካታ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል። ከእነዚህ ሥራዎች መካከል በቅድመ መከላከልና የሥልጠና ዘርፍ በኩል ጎብረተሰቡ ለደንብ መተላለፍ እንዳይዳረግ የባለሥልጣኑን ደንቦች፣ አዋጆች እና መመሪያዎች ምን እንደሆኑ እንዲሁም ደንብ መተላለፍን ተግባራዊ ያደረገ አካል ምን አይነት እርምጃ እንደሚወሰድበትና በገንዘብ ምን ያህል እንደሚቀጣ በተለያዩ አካባቢዎች በመገኘት የግንዛቤ ማስጨበጥ ተግባር ይከናወናል። በቁጥጥርና እርምጃ አወሳሰድ ዘርፍ ደግሞ የደንብ መተላለፎች እንዳይኖሩ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፤ በክትትሉ ደንብ ተላልፈው የተገኙ ደግሞ በደንብ ቁጥር 150/2015 በተቀመጠው የቅጣት ደንብ መሠረት አስተማሪ ቅጣት ይጣልባቸዋል።

ባለሥልጣኑ በእነዚህ በሁለት ዘርፎች ያከናወናቸውን ተግባራት፣ የማዕከል ኃላፊዎችና ዳይሬክተሮች እንዲሁም የክፍለ ከተማ እና ወረዳ ደንብ ማስከበር ኃላፊዎች በተገኙበት የዘጠኝ ወር የሥራ አፈጻጸሙን ሚያዚያ 4 ቀን 2016 ዓ.ም. ገምግሟል። ሲገመግምም፣ በእነዚህ ሁለት ዘርፎች የተሠሩ መልካም ሥራዎች እንዲሁም የታዩ ክፍተቶችን በመለየት ለቀጣይ ሥራ የትኩረት አቅጣጫ በማስቀመጥ ነው።

የሥራ አፈጻጸሙን በውስጥ ባለ አካል ብቻ ሳይሆን የሚገመግመው፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በየሩብ ዓመቱ እየተገናኘ ይገመግማል። በዚህም ባለሥልጣኑ ያለውን መልካም ተሞክሮ አስፍቶ በመሄድ ያለበትን ክፍተት ተመልክቶ ደግሞ ለማስተካከል ግብዓት እየሆነው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ከሃያ ሦስት ባለድርሻ አካላት ጋር በየሦስት ወሩ ከሚያደርገው ቅንጅታዊ የሥራ አፈጻጸም ግምገማ በተጨማሪ ሚያዚያ 10 ቀን 2016 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ እና ከአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ጋር በመተባበር «ፅዱና ምቹ አዲስ አበባን ለመፍጠር የተቋማት ቅንጅታዊ ስምሪት ያለው ፋይዳ» በሚል መሪ ቃል የፓናል ውይይት አድርጓል።

በመድረኩ ላይ የተለያዩ የጎብረተሰብ ክፍሎች፣ የባለሥልጣኑ እና የኤጀንሲው ከፍተኛ አመራሮችና የክፍለ ከተማ ኃላፊዎች፣ አርቲስቶች፣ የፅዳት አምባሳደሮች ተገኝተዋል። ሁለቱም ተቋማት ለመወያያ የሚረዳ ሰነድ ካቀረቡ በኋላ ተሳታፊዎቹ በቀረቡት ሰነዶች ላይ ተወያይተዋል።

በፓናል ውይይቱ ላይ የውይይት መነሻ ሰነድ ያቀረቡት የባለሥልጣኑ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ አበባ እሸቴ እንዳሉት፣ በከተማዋ የደንብ መተላለፎች እንዲቀንሱ ከባለሥልጣኑ ጋር የሚሠሩ ባለድርሻ አካላት ወሳኝ በመሆናቸው ከፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ጋር በቅንጅት እንደተሠራና ውጤትም እንደተገኘ አንስተዋል። የሚስተዋሉ ጉድለቶችም በየደረጃው ተስተካክለው፣ የሁለቱን ተቋማት ቅንጅታዊ አሠራር የበለጠ ለማጎልበት እንዲቻል በማሰብ መድረኩ እንደተዘጋጀ ገልጸዋል። ውይይቱንም በሚዲያዎች አማካኝነት ተደራሽ በማድረግ የጎብረተሰቡን ግንዛቤ በማስፋት እያንዳንዱ ሰው የበኩሉን ኃላፊነትና ግዴታ እንዲወጣ የማስቻል ዓላማ እንዳለውም አስምረውበታል።

አያይዘውም የደንብ ቁጥር 150/2015 ስድስት ዐቢይ የሆኑ የቅጣት ሰንጠረዦች ያሉት ሲሆን፣ ከስድስቱ አንዱ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ የቅጣት ሰንጠረዥ መሆኑን ጠቅሰዋል። ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ በተመለከተ 50 የቅጣት ዓይነቶች የተዘረዘሩ መሆናቸውን በማንሳት በግለሰብ ደረጃ በትንሹ ከብር 50 እስከ 20 ሺህ እና በድርጅት ደረጃ ከብር 1 ሺህ እስከ ብር 20 ሺህ መደንገጉን አስረድተዋል።

ከዚህ በመነሳት ባለሥልጣኑ በተያዘው በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት ጎብረተሰቡን ግንዛቤ በማስጨበጥ በኩል የተለያዩ አደረጃጀቶች እንዲሁም የብሎክ አደረጃጀቶችን በመጠቀም ቤት ለቤት በመዘዋወር፣ የቡና ጠጡና የንቅናቄ መድረኮችን በማዘጋጀትና በመኖሪያ ቤቶችና በትምህርት ቤቶች በመዘዋወር ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻን ጨምሮ በዘጠኙም ደንብ መተላለፎች ላይ ለ2 ሚሊዮን 251 ሺህ 491 የጎብረተሰብ ክፍል ግንዛቤ ፈጥሯል።

በሁሉም ከፍለ ከተማና በአብዛኛው ወረዳ በሞንታርቦ የማስተማር ሥራዎች ተሠርተዋል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ የሚበዛባቸው አካባቢዎችን በመለየት እራሱን አስችሎ ለ585ሺህ 752 ያህል የጎብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል።

ግንዛቤ ተፈጥሮላቸው መስተካከል ያልቻሉ 457ሺህ 852 የደንብ ተላላፊዎች ላይ በደንቡ መሠረት እንዲቀጡና ተጠያቂ እንዲሆኑ ተደርጓል። ከዚህ ውስጥም 4 ሺህ 57ቱ በደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ላይ ደንብ የተላለፉና በገንዘብ የተቀጡ ናቸው። ከእነዚህ ዘጠኙም ደንብ ተላላፊዎች አጠቃላይ 34ሚሊዮን 873ሺህ 563 ብር በቅጣትና ከተወረሰ ንብረት ሽያጭ ለፋይናንስ ገቢ የተደረገ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ደግሞ ብር 2ሚሊዮን 9ሺህ 350 የሚሆነው በደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ደንብ ተላላፊዎች ላይ የተፈጸመ ነው።

ምክትል ሥራ አስኪያጇ እንደገለጹት፣ ከፅዳት አስተዳደር የግንዛቤ ባለሙያዎች ጋር የደንብ ማስከበር የቅድመ መከላከል ኦፊሰሮች በየቀጣናው የሚያደርጉት የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ የግንዛቤ ማስረጽ ተግባር የተሻለ ነው። ሕገወጥ ተግባር ሲኖር ደግሞ ተቀናጅቶ ውሳኔ አብሮ በመስጠት ሕገወጥ ተግባሩ ላይ እርምጃ እንዲወሰድና እንዲስተካከል ጥረት መደረጉ እንዲሁም ፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ የፅዳት ዘመቻ በሚያደርግበት ጊዜ የደንብ ማስከበር ሠራተኞች ፅዳት ዘመቻው ላይ በመገኘት ፅዳቱን በጋራ የማፅዳት ሥራ መሠራቱ በጠንካራ ጎን የሚነሳ ነው።

ይሁን እንጂ፣ በየቀጣናው ላሉ ስለሕገወጥ ፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻ ግንዛቤ ቢፈጠርም በሚፈለገው ልክ ውጤት አለመምጣቱ፤ የቅንጅት ሥራው በየጊዜው አለመገምገም፤ በጋራ የሚሠሩ ሥራዎች ወቅታዊ እንጂ ቋሚ አለመሆን፤ በሁሉም ወረዳዎች በእኩል ሁኔታ ተግባራቱ አለመፈጸማቸውና ተግባራቱ ላለመፈጸማቸው አንዱ ተቋም በሌላው ላይ ማሳበቡ፤ የታዩ ክፍተቶች ሆነው ተመዝግበዋል። እነዚህም ለቀጣይ መስተካከል የሚገባቸው ናቸው።

በመጨረሻም የሁለቱም ተቋም ግብ ከተማዋን ፅዱና ውብ በማድረግ ለሌሎች ተምሳሌት ሆና ማሳየት ስለሆነ ቅንጅታዊ ሥራውን ለማጠናከር በወረዳ ደረጃ የጋራ መድረክ እንዲዘጋጅ ወይዘሮ አበባ ጠይቀዋል።

ከተሳታፊዎች ደግሞ በተደጋጋሚ የተነሳውና ትኩረት ሊሰጠው ይገባል የተባለው ጉዳይ ቅንጅታዊ ሥራን በማጠናከር ለጎብረተሰቡ በተከታታይ ባለመሰልቸት ግንዛቤ መስጠቱ ላይ ተግቶ መሥራት እንደሚገባ፤ እንዲሁም ጎብረተሰቡ ፍቃደኛ ሆኖ በፅዳት ሥራ ላይ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ ነው።

የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ በማጠቃለያ ንግግራቸው ከጎብረተሰቡ የተነሱት ሀሳቦችን ለቀጣይ ሥራዎች ግብዓት ተደርገው እንደሚወሰዱ ጠቅሰው ከተማዋን "ስማርት ሲቲ" ለማድረግ ባለሥልጣኑ የራሱን ድርሻ እንደሚወጣ ገልጸዋል። የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስኪያጅ ዶክተር እሸቱ ለማም የታዩት መልካም ጎኖች እንደሚቀጥሉ፣ ክፍተቶችን ለማስተካከልም ደግሞ የተጠየቀው የጋራ መድረክ እንደሚዘጋጅ አንስተዋል።